# ዘዘካርያስ ነቢይ።

## መቅድም፡

ዘካርያስ፡ ማለት፡ ዝኩር፡ ዝክረ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው። ነገዱ፡ ከነገደ፡ ሌዊ፡ ነው። አባቱ፡ በራክዩ፡ ሀዶ፡ አያቱ፡ ነው። አንድም፡ ሀዶ፡ እናቱ፡ ናት፤ በእግዚአብሔር፡ ቸርነት፤ በቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ተራዳኢነት፡ የወጡ፡ እስራኤል፡ እንዳልወጡ፡ ሁነው፡ እያያቸው፡ ተናግሯል፤ ይህ፡ አርእስት፡ ነው። ሠለስቱ፡ ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡ አርዕስት፡ ሲሰጡ፡ ሰጥተውታል፤ እርሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ በካልዕ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ብሎ፡ ያመጣዋል።

## ምዕራፍ ፩

፩። በካልዕ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለዳርዮስ፡ በሳምን፡ ወርኁ፡ ኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ዘካርያስ፡ ወልደ፡ በራክዩ፡ ወልደ፡ ሀዶ፡ ነቢይ፤

ዳርዮስ፡ በነገሠ፡ በሁለተኛ፡ ዘመን፡ የዘሩባቤል፡ አልጸናምና፡ በዳርዮስ፡ ቆጠረ፤ በስምንተኛ፡ ወር፡ በኅዳር፡ ከበራክዩ፡ ልጅ፡ ከዘካርያስ፡ ዘንድ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር መጣ፡ ተነገረ።

፪። ወይቤሎ፡ ተምዐ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕለ፡ አበዊክሙ፡ ዓቢየ፡ መዓተ፤

እግዚአብሔር፡ በአባቶቻችሁ፡ ላይ፡ ፈጽሞ፡ ፈረደ፡ አለው።

፫። ወበሎሙ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ በላቸው።

ተመየጡኦ፡ ኀቤየ፡ ወአነኒ፡ እትመየጥ፡ ኀቤክሙ፤

እናንተ፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ ወደኔ፡ ተመለሱ፤ ብትመለሱ፡ እኔም፡ ከመዓት፡ ወደምሕረት፡ እመለስላችኋለሁ፡ አለ፡ በላቸው፡ ሲል፡ ከዘካርያስ፡ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ መጣ፡ ተነገረ። አንድም፡ ብትመለሱ፡ እመለስላችኋለሁ፡ አለ፡ የሚል፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ መጣ፡ ተነገረ።

፬። ወኢትኩኑ፡ ከመ፡ አበዊክሙ፡ እለ፡ ገሠጽዎሙ፡ ነቢያት፡ ቀደምት፤

የቀደሙ፡ ነቢያት፡ እንደገሠጿቸው፤ እንዲህ፡ እንዳሏቸው፤ እንደ፡ አባ



ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ እንዳሏቸው።

ተመየጡ፡ እምፍኖትክሙ፡ እኩይ፤

ከክፉ፡ ሥራችሁ፡ ተመለሱ።

ወእምእከየ፡ ምግባሪክሙ፤

ከስርቆት፡ ከቅሚያ፡ ተመለሱ፡ እንዳሏቸው፡ እንዳባቶቻችሁ፡ አትሁኑ፡ ሲል፡ መጣ፡ ተነገረ።

ወአበዩ፡ ሰሚዖትየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ የኔን፡ ቃል፡ መስማት፡ እምቢ አሉ፡ እንዳሏቸው፡ እንዳባቶቻችሁ፡ አትሁኑ፡ ሲል፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ከዘካርያስ፡ ዘንድ መጣ፡ ተነገረ።

፭። አይቴኑ፡ አበዊክሙ፡ ወነቢያቲክሙ፤

አባቶቻችሁ፡ ነቢያትስ፡ ወዴት፡ አሉ?

ርእዩ፡ እመ፡ ሀለዉ፡ ይእዜ፤

ዛሬ፡ አሉ፡ እንደሆነ፡ አስተውሉ፤

፮። ወይእዜኒ፡ ተወከፉ፡ ቃልየ፡ ወሕግየ፤

አሁንም፡ ነገሬን፡ ሕጌን፡

ዘአዘዝኩ፡ በመንፈስየ፡ ለአግብርትየ፡ ነቢያት፡ ቀደምት፡ እለ፡ ረከብዎሙ፡ ለአበዊክሙ፤

መንፈስ፡ ቅዱስን፡ መምህር፡ በማድረግ፡ አባቶቻችሁን፡ ያገኟቸው፡ በቀደሙ፡ ነቢያት፡ ያዘዝሁትን፡ ተቀበሉ።

ወተሰጥውዎሙ፡ ወይቤልዎሙ፤

መለሱላቸው፤ እንዲህ፡ አሏቸው።

በከመ፡ ነበበ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፡ ከመ፡ ይግበር፡ ላዕሌነ፤ በከመ፡ ፍናዊነ፡ ወበከመ ጌጋይነ፡ ከማሁ፡ ይግበር፡ ላዕሌነ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንደሥራችን፡ እንደበደላችን፡ መጠን፡ በኛ፡ ላይ፡ ያደርገው፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ እንደተናገረ፡ ያድርግልን።

፯። ወአመ፡ እስራ፡ ወረቡዑ፡ ለወርኃ፡ ሳባጥ፤

የካቲት፡ በባተ፡ በሀያ፡ አራት፡ ቀን።

አመ፡ ተስዑ፡ ለጽልመት፤

ጨረቃ፡ ብርሃኗን፡ ባጣች፡ ሕፀፅ፡ ባደረገች፡ በዘጠኝ፡ ቀን።

በካልዕ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለዳርዮስ፤

ዳርዮስ፡ በነገሠ፡ በሁለተኛ፡ ዘመን።


www.ethiopianorthodox.org

ኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ዘካርያስ፡ ወልደ፡ በራክዩ፡ ወልደ፡ ሀዶ፡ ነቢይ፤

ከሀዶና፡ ከበራክዩ፡ ልጅ፡ ከዘካርያስ፡ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል መጣ፡ ተነገረ፤

፰፤ ወደቤ፡ ርእኩ፡ በሌሊት፡ ብእሴ፡ ይጼዐን፡ ዲበ፡ ፈረስ፡ ቀይህ፤

ሌሊት፡ በሐመር፡ ፈረስ፡ የተቀመጠ፡ ሰው፡ አየሁ፤ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ነው፤ የባቢሎንን፡ ሰዎች፡ ደም፡ አፈስሳለሁ፡ ሲል፡ በሐመር፡ ፈረስ፡ ላይ፡ ተቀምጦ፡ ይታየዋል፤

ወይቀውም፡ ማዕከለ፡ ክልዔቱ፡ አዕዋም፡ ዘአዲሽም፡ ዘቦ፡ ጽላሎት፤

ጥላ፡ ባለው፡ ጽኑ፡ በሆነ፡ ዋርካ፡ ወይራ፡ መካከል፡ ቁሞ፡ አየሁት፡ ማለት፡ በቂሮስና፡ በዳርዮስ፡ መካከል፤ አንድም፡ በዮሴዕና፡ በዘሩባቤል፡ መካከል፡ አየሁት፤

ወድኅሬሁ፡ አፍራስ፡ ቀይሐን፤

በኋላውም፡ በሐመር፡ ፈረስ፡ የተቀመጡ፡ ሰዎች፡ አየሁ፤ እሊህም፡ መላእክት፡ ናቸው፤ የባቢሎንን፡ ሰዎች፡ ደም፡ እናፈሳለን፡ ሲሉ፡ በሐመር፡ ፈረስ፡

ወጸሊማን፤

በዱሪ፡ ፈረስ፡ የተቀመጡ፡ ሰዎች፡ አየሁ፤ እኒህም፡ መላእክት፡ ናቸው፤ በባቢሎን፡ ሰዎች፡ መከራ፡ እናመጣለን፡ ሲሉ፡ በጥቁር፡ ፈረስ፡ ተቀምጠው፡ ያያቸዋል፤

ወኵሳኵሳን፤

በጥርኝ፡ ፈረስ፡ የተቀመጡ፡ ሰዎች፡ አየሁ፤ ሕዝብና፡ አሕዛቡ፡ ተጋብተው፡ የተወለዱ፡ ናቸው፤

ወፀዓድው፤

በአምባላይ፡ ፈረስ፡ የተቀመጡ፡ ሰዎች፡ አየሁ፤ እነዚህም፡ መላእክት፡ ናቸው፤ ለእስራኤል፡ ተድላ፡ ደስታ፡ እናደርጋለን፡ ሲሉ፡ በአምባላይ ፈረስ፡ ተቀምጠው፡ ያያቸዋል፤

፱፤ ወዕቤሎ፡ ምንትኑ፡ እሉ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ እሊህ፡ ምንድናቸው፡ አልሁት፤

ወይቤለኒ፡ መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፤

የሚናገረኝ፡ ባልደረባዬ፡ መልአክ፡ እንዲህ፡ አለኝ፤

አነ፡ እነግረከ፡ ከመ፡ ምንት፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፤

ይህ፡ [illegible]



፲፤ ወተሰጥወኒ፡ ብእሲ፡ ዘይቀውም፡ ማዕከለ፡ ፪ዔ፡ አዕዋም፡ ዘአዲሽም፡ ማዕከለ፡ አድባር፤

በዮሴዕና፡ በዘሩባቤል፡ ያደረ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ በቂሮስና፡ በዳርዮስ፡ መካከል፡ መለሰልኝ፤

ወይቤለኒ፡ እሉ፡ እሙንቱ፡ እለ፡ ፈነወሙ፡ እግዚአብሔር፡ ይዑድዋ፡ ለምድር፤

ባቢሎንን፡ ያጠፏት፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ የላካቸው፡ ናቸው፡ አለኝ፤

፲፩፤ ወተሰጥዎ፡ ለመልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ዘይቀውም፡ ማዕከለ፡ ፪ዔ፡ አዕዋም፡ ዘአዲሽም፤

በቂሮስና፡ በዳርዮስ፡ ያደረ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ባልደረባዬ፡ መልአክን፡ እንዲህ፡ አለው፤

ወይቤሉ፡ ዖድነ፡ ኵላ፡ ምድረ፤

አገሩን፡ ሁሉ፡ ዞርን፤

ወናሁ፡ ኵላ፡ ምድር፡ ትነብር፡ ወታረምም፤

እነሆ፡ ከኢየሩሳሌም፡ በቀር፡ አገሩ፡ ሁሉ፡ ፀጥ፡ ብሏል፡ አሉ፤

፲፪፤ ወተሰጥወ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፤

ባልደረባዬ፡ መልአክ፡ መለሰ፤

ወይቤ፡ እግዚእ፡ ዘኵሎ፡ ትመልክ፤

[illegible]

እስከ፡ ማዕዜኑ፡ ኢትሣሃላ፡ ለኢየሩሳሌም፡ ወለአህጉረ፡ ይሁዳ፡ ዘአስተትካ፡ እምዝ፡ ፸፡ ዓም፤

ከሰባ፡ ዘመን፡ ከመጀመሪያው፡ ጀምሮ፡ የናቅሃት፡ ያቀለልሃት፡ ኢየሩሳሌምን፡ ይቅር፡ የማትላት፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፤ የይሁዳንስ፡ አውራጃ፡ ይቅር፡ የማትላት፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፤

፲፫፤ ወተሰጥዎ፡ እግዚአብሔር፡ ለዝኩ፡ መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፡ ቃለ፡ ሠናየ፡ ወነገረ፡ ፍሥሓ፤

እግዚአብሔር፡ ለሚነግረኝ፡ መልአክ፡ በጎ፡ ነገር፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ ነገር፡ መለሰለት፤

፲፬፤ ወይቤለኒ፡ ዝኩ፡ መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፡ ክላህ፡ ወበል፤

የሚነግረኝ፡ ባልደረባዬ፡ መልአክ፡ አሰምተህ፡ ተናገር፡ አለኝ፤

ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ቀናዕኩ፡ ላዕለ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወላዕለ፡ ይሁዳ፡ ዓቢየ፡ ቅንዓተ፤

በኢየሩሳሌምና፡ በይሁዳ፡ አሕዛብ፡ መከራ፡ ስላጸኑባቸው፡ ፈጽሜ፡ ቀናሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭። ወተማዕኩ፡ ሳዕለ፡ አሕዛብ፡ ዓቢየ፡ መዓተ፡ እለ፡ ተቃወሙ።

እስራኤልን፡ በሚቃወሙ፡ በአሕዛብ። አንድም፡ ሕግን፡ በሚቃወሙ፡ በአሕዛብ፡ ፈጽሜ፡ ፈረድሁ።

ሶበ፡ አነ፡ ተማዕኩ፡ ኅዳጠ፡ ወእሙንቱሰ፡ ወሰኩ፡ እኪተ፡ በዲበ፡ እኪት።

እኔ፡ ጥቂት፡ መከራ፡ ባመጣ፡ እነሱ፡ ግን፡ በመከራ፡ ላይ፡ መከራ፡ አምጥተውባቸዋልና፡ ለጌታ፡ የመቃብያን፡ መማረክ፡ ፈቃዱ፡ ነው። እነዚያ፡ ግን፡ አትርፈው፡ ለሴት፡ ለመሸታ፡ ሸጠዋቸዋልና።

፲፮። በእንተ፡ ዝንቱ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ስለዚህ፡ ነገር፡ እንዲህ፡ አለ።

እትመየጣ፡ ለኢየሩሳሌም፡ በምሕረት።

ኢየሩሳሌምን፡ ከመዓት፡ ወደ ምሕረት፡ እመለስላታለሁ፡ አለ።

ወይትሐነፅ፡ ቤትየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ማደሪያዬ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ይሠራል፡ አለ።

ወእሣርር፡ መሠረታ፡ ለኢየሩሳሌም።

የኢየሩሳሌምን፡ መሠረቷን፡ አጸናለሁ።

፲፯። ወዓዲ፡ ይቤለኒ፡ መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፡ ክላሁ፡ ወበል።

ዳግመኛ፡ የሚነግረኝ፡ ባልደረባዬ፡ መልአክ፡ እንዲህ፡ ብለህ፡ አስተምር፡ አለኝ።

ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ።

ወዓዲ፡ ትትከዓው፡ ሠናይት፡ ውስተ፡ አህጉር።

ዳግመኛ፡ በሀገሩ፡ ሁሉ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይደረጋል። አንድም፡ ትምህርት፡ ረድኤት፡ ይሰጣል።

ወይሣሃላ፡ እግዚአብሔር፡ ለጽዮን።

ጽዮንን፡ እግዚአብሔር፡ ይቅር፡ ይላታል።

ወዓዲ፡ የኃርያ፡ ለኢየሩሳሌም።

ዳግመኛ፡ እግዚአብሔር፡ ኢየሩሳሌምን፡ ይወዳታል።

፲፰። ወካዕበ፡ አንሣዕኩ፡ አዕይንትየ፡ ወርኢኩ፡ አርባዕተ፡ አቅርንተ።

ዳግመኛ፡ በአእምሮ፡ አንገቴን፡ አቅንቼ፡ አራቱን፡ ነገሥተ፡ አሕዛብ፡ አየሁ፡ በአራቱ፡ ሊቃነ፡



መላእክት፡ ምግብና፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ አሕዛብ፡ ሲነግሡ፡ ያያል።

፲፱። ወዕቤሎ፡ ለዝኩ፡ መልአክ፡ ዘይ ትናገረኒ፡ ምንትኑ፡ ዝንቱ፡ እግዚኦ፡

የሚናገረኝ፡ ባልደረባዬ፡ መልአኩን፡ አቤቱ፡ ይኸ፡ ምንድ ነው፡ አልሁት።

ወይቤለኒ፡ እሉ፡ አቅርንት፡ እለ፡ ይዘርእዎሙ፡ ለይሁዳ፡ ወለእስራኤል።

እነዚህም፡ ዐሥሩን፡ ነገድ። ሁለቱን፡ ነገድ፡ የሚበትኑ፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ አሕዛብ፡ ናቸው፡ አለኝ።

፳። ወካዕበ፡ አርአየኒ፡ እግዚአብሔር፡ አርባዕተ፡ ፀረብተ።

ዳግመኛ፡ እግዚአብሔር፡ የሚስሉ፡ አራቱን፡ ሊቃነ፡ መላእክት፡ አሳየኝ። አራቱ፡ ሊቃነ፡ መላእክት፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ አሕዛብን፡ ይዘው፡ ሲመጡ፡ ያያል።

፳፩። ወእቤሎ፡ ምንተኑ፡ ይገብሩ፡ መጽኡ፡ እሉ።

እሊህ፡ አራቱ፡ ሊቃነ፡ መላእክት፡ ምን፡ ሊአደርጉ፡ መጡ፡ [illegible]

ወይቤለኒ፡ እስመ፡ ከፍዑ፡ እሉ፡ አቅርንት፡ እለ፡ ይዘርውዎሙ፡ ለይሁዳ፡ ወለእስራኤል።

ዐሥሩን፡ ነገድ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ የሚበታትኗቸው፡ አሕዛብ፡ ደክመዋልና።

ወአልቦ፡ዘአንሥአ፡ርእሶ፡እምኔሆሙ።

ከአሕዛብ፡ ሥልጣኑን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደረገ፡ የለምና።

ወመጽኡ፡ ከመ፡ ያብልኅዎሙ፡ በእደዊሆሙ።

አሕዛብን፡ በሥልጣናቸው፡ ይስቧቸው፡ ዘንድ፡ መጡ። አንድም፡ እስመ፡ ከፍዑ። እስራኤል፡ ከፍ ተዋልና፡ ማለት፡ ኃጢአት፡ ሠር ተዋል። ጣዖት፡ አምልከዋልና። ከእስራኤል፡ ሥልጣኑን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደረገ፡ የለምና። ዐሥሩን፡ ነገድ። ሁለቱን፡ ነገድ፡ የሚበታትኗቸው፡ እሊህ፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ አሕዛብ፡ እስራኤልን፡ በእጃቸው፡ ይጥሏቸው፡ ዘንድ፡ መጡ። ከእስራኤልም፡ ሥልጣኑን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደረገ፡ የለም። አንድም፡ ዐሥሩን፡ ነገድ። ሁለቱን፡ ነገድ፡ የሚበታትኗቸው፡ አሕዛብ፡ ከፍተዋልና።

www.ethiopianorthodox.org

ከአሕዛብ፡ ወገን፡ ሥልጣኑን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደረገ፡ የለምና፡ በእስራኤል፡ እጅ፡ ይጥሏቸው፡ ዘንድ፡ መጡ፤

እሉ፡ እንከ፡ ፬ቱ አቅርንተ፡ አሕዛብ፡ እሙንቱ፡ እለ፡ አንሥኡ፡ ቀርኖሙ፡ ይዝርውዋ፡ ለምድረ፡ እግዚአብሔር፤

እሊህም፡ ኢየሩሳሌምን፡ ያጠፏት፡ ዘንድ፡ ሥልጣናቸውን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደረጉ፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ አሕዛብ፡ ናቸው።

## ምዕራፍ ፪

### ጉባኤ

፩፤ ወካዕበ፡ አንሣዕኩ፡ አዕይንትየ፤

ዳግመኛ፡ አንገቴን፡ አቅንቼ፡ አየሁ፤

ወርኢኩ፡ ነዋ፡ ብእሲ፡ ወውስተ፡ እዴሁ፡ ሐብለ፡ መሥፈርት፤

ዘሩባቤልን፡ አየሁ፤ በዘሩባቤል፡ በእጁ፡ ርስት፡ የሚያካፍልበት፡ ገመድ፡ አለ፤ አንድም፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ የሚሠራበት፡ ሥልጣን፡ አለው፤

፪፤ ወዕቤሎ፡ አይቴ፡ ተሐውር፡ አንተ፤

አንተ፡ ወዴት፡ ትሄዳለህ?

ወይቤለኒ፡ ከመ፡ እስፍራ፡ ለኢየሩሳሌም፤

ኢየሩሳሌምን፡ እሰፍራት፡ ዘንድ፡ እሄዳለሁ፡ አለኝ፤

ወአእምር፡ ሚመጠን፡ ኑኃ፡ ወሚመጠን፡ ራኅባ፤

ወርዷ፤ ቁመቷ፡ ምን፡ እንደ ሆነ፡ አውቅ፡ ዘንድ፡ እሄዳለሁ፤

፫፤ ወእንዘ፡ ይቀውም፡ ገዢኩ፡ መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፤

የሚነግረኝ፡ ባልደረባዬ፡ መልአክ፡ ቁሞ፡ ሳለ፤

መጽአ፡ ካልዕ፡ መልአክ፤

ሌላ፡ መልአክ፡ መጣ፤

ወተቀበሎ፤

ባልደረባዬ፡ መልአክ፡ ወጥቶ፡ ተቀበለው፤

፬፤ ወይቤሎ፡ መልአክ፡ ሩዕ፡ ወበሎ፡ ለዝኩ፡ ወሬዛ፤

ፈጥነህ፡ ሄደህ፡ ዘካርያስን፡ እንዲህ፡ በለው፤

ዘእንበለ፡ ፍሬኑ፡ ትነብር፡ ኢየሩሳሌም፡ እምብዙኃ፡ ሰብእ፡ ወእንስሳ፡ ዘማዕከላ፤

ከብዙ፡ ሰው፤ ከብዙ፡ እንስሳ፡ ተለይታ፡ ኢየሩሳሌም፡ ያለ፡ ልጅ፡ የምትቀር፡ ይመስልሃል?



ተለይታ፡ ያለ፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ የምትቀር፡ ይመስልሃል?

፭፤ ወአነ፡ እከውና፡ ጥቅመ፡ እሳት፡ ዓውዳ፡ ወእከውና፡ ክብራ፡ በማዕከላ፡

ኢየሩሳሌምን፡ ዳሯ፡ እሳት፡ መካከሏ፡ ገነት፡ ይሁን፡ እንድትባል፡ አደርጋታለሁ፤

፮፡ ጉዩ፡ እምብሔረ፡ ሰሜን፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ከፋርስ፡ ከባቢሎን፡ ውጡ፡ አለ፤

እስመ፡ እምአርባዕቱ፡ ነፋሳተ፡ ሰማይ፡ አስተጋባእኩሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ውስተ፡ ጽዮን፤

ካራቱ፡ ማዕዘን፤ አንድም፡ ከአራቱ፡ አህጉር፡ እግዚአብሔር፡ በጽዮን፡ እሰበስባችኋለሁ፡ ብሏልና፡ ጉዩ፡ አለ፤

፯፤ ወይድኅኑ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስተ፡ ባቢሎን፤

በሚጠት፡ ያመኑ፡ አሕዛብ፡ ይድናሉ፤ አንድም፡ በባቢሎን፡ የነበሩ፡ እስራኤል፡ ይድናሉ፤

፰፤ እስመ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ

ወየአምሩ፡ ከመ፡ ፈነወኒ፡ እግዚአብሔር፡ ድኅረ፡ ስብሐቲሁ፤

እግዚአብሔር፡ ብርሃኑን፡ በደብረ፡ ሲና፡ ከገለጠ፡ በኋላ፤ አንድም፡ በሚጠት፡ ጌትነቱን፡ ከገለጠ፡ በኋላ፡ እንደላከኝ፡ ያውቃሉ፤

ወዘኵሉ፡ ዘገሠሠክሙ፡ በእኩይ፡ ይትገሠሥ፡ በእንተ፡ አዕይንቲሁ፤

ጥቂት፡ መከራ፡ ያመጣባችሁ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ጽኑ፡ መከራ፡ ይመጣበታል፤

፱፤ ወናሁ፡ አነ፡ አመጽእ፡ እዴየ፡ ላዕሌሆሙ፤

እነሆ፡ እኔ፡ በላያቸው፡ እደ፡ መዓቴን፡ አመጣባቸዋለሁ፤

ወይከውኑ፡ ሕብልያ፡ ለእለ፡ ተቀንዩ፡ ሎሙ፤

ለሚገዙላቸው፡ ለቂሮስ፡ ለዳርዮስ፡ ብዝበዛ፡ ይሆናሉ፤ አንድም፡ ይገዟቸው፡ ለነበሩ፡ ለእስራኤል፡ ብዝበዛ፡ ይሆናሉ፤

ወየአምሩ፡ ከመ፡ ፈነወኒ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንደላከኝ፡ ያውቃሉ፤

፲፤ ተፈሥሒ፡ ወተሐሠዪ፡ ወለተ፡ ጽዮን፤

የጽዮን፡ ልጅ፡ በአፍአ፡ በውስጥ፡ ደስ፡ ይበልሽ፤ አንድም፡

www.ethiopianorthodox.org

የጽዮን፡ ልጅ፡ ምእመን፡ ደስ፡
ይበልሽ፤

እስመ፡ ናሁ፡ አነ፡ እመጽእ፡ ወአኃ
ድር፡ ማዕከሌኪ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ እነሆ፡ እኔ፡
መጥቼ፡ በመካከልሽ፡ በረድኤት፡
አድራለሁ፡ ብሏልና፤ አንድም፡
ሰው፡ እሆናለሁ፡ ብሏልና፤

፲፩፤ ወይመጽኡ፡ ብዙኃን፡ አሕ
ዛብ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ይእተ፡ አሚረ፤

ያን፡ ጊዜ፡ በሚጠት፡ ያመኑ፡
ብዙ፡ አሕዛብ፡ ይመጣሉ፤

ወይከውንዎ፡ ሕዝቦ፤

ወገኖቹ፡ ይሆናሉ፤ አንድም፡
ያን፡ ጊዜ፡ በዘመነ፡ ሐዲስ፡ ብዙ፡
አሕዛብ፡ አምነው፡ ይመጣሉ፤
ወገኖቹ፡ ይሆናሉ፤

ወይነብሩ፡ ማዕከሌኪ፤

በመሐከልሽ፡ ይኖራሉ፤

ወተአምሪ፡ ከመ፡ ፈነወኒ፡ ኀቤኪ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ወደ፡ አንቺ፡ እንደላከኝ፡
ታውቂያለሽ፤ አንድም፡ ሰው፡
እንደሆንኩ፡ ታውቂያለሽ፤

፲፪፤ ወይወርሶ፡ እግዚአብሔር፤
ለይሁዳ፡ መክፈልቶ፡ በምድር፡ ቅድስት፤

በከበረች፡ አገር፡ በኢየሩሳሌም፡
እግዚአብሔር፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡
ገንዘብ፡ ያደርጋቸዋል፤ አንድም፡
ያወርሶ፡ ይላል፤ ለይሁዳ፡ ዕፃ
ውን፡ የጠርሰዋል፤

ወዓዲ፡ የኃርያ፡ እግዚአብሔር፡ ለኢ
የሩሳሌም፤

ዳግመኛ፡ እግዚአብሔር፡ ኢየ
ሩሳሌምን፡ ይመርጣታል፤

፲፫፤ ወይፈርህ፡ ኵሉ፡ ዘነፍስ፡
እምቅድመ፡ ገጹ፡ ለእግዚአብሔር፤

ከእግዚአብሔር፡ ከገጸ፡ መዓቱ፡
የተነሣ፡ ከሥጋ፡ ከነፍስ፡ የተ
ፈጠረ፡ ሁሉ፡ ይፈራል፤

እስመ፡ ተንሥአ፡ እማኅደረ፡ መቅደሱ፤

ከመመስገኛው፡ ቦታ፡ በረድኤት፡
ተነሥቷልና።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ወአርአየኒዮ፡ እግዚአብሔር፡
ለካህን፡ ዓቢይ፡ ይቀውም፡ ቅድመ፡ ገጹ፡
ለመልአከ፡ እግዚአብሔር፤

ደጉን፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ዮሴዕን፡
በመልአኩ፡ ፊት፡ ቁሞ፡ አየሁት፤

ወይቀውም፡ ሰይጣን፡ በየማኑ፡ ከመ፡
ያዕቅፎ፤

ያሰናክለው፡ ዘንድ፡ ሰይጣን፡
በፊቱ፡ ቁሞ፡ አየሁት፤

፪፤ ወይቤሎ፡ መልአከ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ለሰይጣን፡ ለያኅሥርከ፡ እግዚ
አብሔር፡ ዘኃረያ፡ ለኢየሩሳሌም፤

መልአኩ፡ ሰይጣንን፡ እንዲህ፡
አለው፤ ኢየሩሳሌምን፡ የመረጣት፡
እግዚ አብሔር፡ የጐሰቁልህ፡



አለው፤ እንደርግማን፤ አንድም፡
እግዚአብሔር፡ ያጐሰቍልሃል፡
ተው፡ አለው፡ እንደምክር፤ አን
ድም፡ የኃሥረከ፡ እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡ ያጐሰቍልሃል፡
አለው፤

ወናሁ፡ ዝንቱ፡ ከመ፡ ትንታግ፡ እሳት፡
ዘእውጽእዎ፡ እምአፍሐም፤

እነሆ፡ ይህ፡ ዮሴዕ፡ ከእሳት፡
ሊይተው፡ እንዳወጡት፡ ትንታግ፡
ሁሉ፡ አልቀው፡ ብቻውን፡
ቀርቷል፤

፫፤ ወዮሴዕኒ፡ ይለብስ፡ አልባሰ፡
ርሱሐ፤

ዮሴዕም፡ ልብሰ፡ ኃዘን፡ ለብሶ፤

ወይቀውም፡ ቅድመ፡ ገጹ፡ ለመልአከ፡
እግዚአብሔር፤

በመልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ፊት፡
ቁሞ፡ ነበር፤

፬፤ ወይቤሎ፡ ለመልአከ፡ ዘይቀ
ውም፡ ቅድመ፡ ገጹ፡ አእትት፡ አልባሰ፡
ርሱሐ፡ እምላዕሌሁ፤

እግዚአብሔር፡ በፊቱ፡ የቆመ፡
መልአኩን፡ እንዲህ፡ አለው፤
ልብሰ፡ ኃዘንን፤ ልብሰ፡ ንዴ
ትን፡ ከላዩ፡ ላይ፡ አርቅለት፤

ወይቤሎ፡ ናሁ፡ አእተትኩ፡ እምኔከ፡
ኃዘነከ፤

እነሆ፡ እኔ፡ ኃዘንህን፡ ካንተ፡
አራቅሁልህ፡ ...

ወአልበስኩከ፡ ጸደሬ፤

ምሉጣ፡ ቀሚስ፡ አለበስሁህ፡
ማለት፡ ደስ፡ አሰኘሁህ፤

፭፤ ወወደዮ፡ ሰበነ፡ ንጹሐ፡ ውስተ፡
ርእሱ፤

በራሱም፡ ኵፌት፡ ደፋለት፤

ወአልበስዎ፡ አልባሰ፤

የመዓርግ፡ ልብስ፡ አለበሱት፤

፮፤ ወቆመ፡ መልአከ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ወአስምአ፡ ሎቱ፡ ለዮሴዕ፤

መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ በግ
ብር፡ መጥቶ፡ ቆመ፤ በዮሴዕ፡
አዳኘበት፤

፯፤ ወይቤሎ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ
ሔር፡ እንዲህ፡ አለው፤

እመ፡ በፍኖትየ፡ ሖርከ፡ ወዓቀብከ፡
ትእዛዝየ፤

በሕጌ፡ ጸንተህ፡ ብትኖር፡ ትእ
ዛዜን፡ ብትጠብቅ፤

ወአንተ፡ ትኴንን፡ ቤትየ፤

ወገኖቼ፡ እስራኤልን፡ አንተ፡
ትገዛለህ፤

ወእመ፡ ዓቀብከ፡ ዐፀድየ፤

ሕጌን፡ ብትጠብቅ፤

እሁብከ፡ ዘይከውነከ፡ በማዕከለ፡ ኵሎሙ፡
እለ፡ ይቀውሙ፡ እምድኅሬከ፤

የሚረባሕ፡ የሚጠቅምህ፡ ሊቀ፡
ካህናትን፡ እሰጥሃለሁ፤ ከአን
ተም፡ በኋላ፡ እንዳንተ፡ የሚ
ሾሙትን፡ ሹመት፡ እሰጥሃለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፤ ስማዕ፡ ዮሴዕ፡ አንተ፡ ወልደ፡ ዮሴዴቅ፡ ካህን፡ ዓቢይ፤

ደጉ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ዮሴዕ፡ የዮሴዴቅ፡ ልጅ፡ አንተ፡ ስማ፤

ወቢጽከ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ቅድመ፡ ገጽከ፤

በፊትህ፡ የሚቆሙ፡ ባልንጀሮችህም፡ ይስሙ፤

እስመ፡ ሰብአ፡ ዓይን፡ እሙንቱ፤

መምህራን፡ ናቸውና፤

ወናሁ፡ አመጽእ፡ ላዕለ፡ ገብርየ፡ ሠረቃዊ፤

ዘሠረፀ፡ እመንግሥት፡ ዘወጽአ፡ እምባቢሎን ሲል፡ ነው፤

፱፤ ወዕብነ፡ እንተ፡ ወሀብኩ፡ ቅድመ፡ ገጹ፡ ለዮሴዕ፤

ለዮሴዕ፡ የሰጠኋትን፡ ደንጊያ፡ ለዘሩባቤል፡ እሰጠዋለሁ፡ ማለት፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ እንዲሠራ፡ አደርገዋለሁ፤ ዕብን፡ ቢል፡ ይችም፡ ለዮሴዕ፡ የሰጠሁት፡ ደንጊያ፡ ናት፤

በዲበ፡ አሐቲ፡ ዕብን፡ ፯ቱ አዕይንት፡ እሙንቱ፤

ለአንዲቱ፡ ደንጊያ፡ ሰባት፡ ዓይን፡ አላት፤ ማለት፡ ለቤተ፡ መቅደስ፡ ዮሴዕ፤ ዘሩባቤል፤ ዕዝራ፤ ነሕምያ፤ ሐጌ፤ ዘካርያስ፤ ሚልክያስ፤ መርዶክዮስ፤ ኢዮስያስ፡ አሏት፤

ወናሁ፡ አነ፡ እከሪ፡ ግበ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ እሠራለሁ፡ አለ፤ ግብ፡ አላት፤ እንደጕድጓድ፡ ያለ፡ አላትና፤ አንድም፡ በአሕዛብ፡ የሚያመጣውን፡ መከራ፡ በጕድጓድ፡ መሰለው፤

ወአገሥሥ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ኃጢአታ፡ ለይእቲ፡ ምድር፡ በአሐቲ፡ ዕለት፤

በኃጢአት፡ ምክንያት፡ ባቢሎንን፡ በአንዲት ቀን፡ በእደ፡ መዓቴ፡ እዳስሳታለሁ፤ አንድም፡ ለኵላ፡ ኃጥእት፡ ይላል፤ ኃጥእት፡ ባቢሎንን፡ አጠፋታለሁ፤

፲፤ ይእተ፡ አሚረ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ኵልክሙ፡ ጸውዑ፡ ቢጸክሙ፡ ታሕተ፡ ወይንክሙ፡ ወታሕተ፡ በለስክሙ፤

እንደ፡ ሰሎሞን፡ ጊዜ፡ በልታችሁ፡ ጠጥታችሁ፡ ከወይኑ፡ ከበለሱ፡ ሥር፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ታደርጉ፡ ዘ...



# ምዕራፍ ፬

፩፤ ወተመይጠ፡ መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፤

የሚናገረኝ፡ መልአክ፡ ካንዱ፡ ነገር፡ ወደ፡ አንዱ፡ ነገር፡ ተመለሰ፤

ወአንቅሐኒ፡ ከመ፡ ሶበ፡ ይነቅሕ፡ ሰብእ፡ እምንዋም፤

ሰው፡ ከእንቅልፉ፡ እንዲነቃ፡ ቀሰቀሰኝ፤

፪፤ ወይቤለኒ፡ ምንተ፡ ትሬኢ፤

ምን፡ ታያለህ? አለኝ፤ ጠፍቶት፡ አይደለም፤ ለማንቃት፡ ለማትጋት፡ ነው፤ አንድም፡ ሊያናግረው፡ ቢወድ፡ ነው፤

ወይቤ፡ ርኢኩ፡ ተቅዋመ፡ ማኅቶት፡ ዘኵለንታሁ፡ ወርቅ፤

ሁለንተናዋ፡ በትሀ፡ ወርቅ፡ የሆነ፡ ተቋምን፡ አየሁ፤

ወማኅቶት፡ ዲቤሁ፤

ፋና፡ በላይዋ፡ ላይ፡ አለ፤

ወ፯ቱ፡ መኃትው፡ ላዕሌሁ፤

ሰባት፡ ምንባረ፡ ፈትል፡ አላት፤ አንድም፡ ሰባት፡ መግላሊት፡ አላት፤

ወ፯ቱ መሳውር፡ ዘያነብሩ፡ ላዕሌሁ፤

ዘ... ሰባት፡

፫፤ ወ፪ቱ፡ አዕፁቀ፡ ዘይት፡ መልዕልቴሁ፤

ሁለት፡ የዘይት፡ ጫፎች፡ በላይዋ፡ ላይ፡ አሉ፤ ከታች፡ በቅሰው፡ በልጠዋት፡ ያያል፤

አሐቲ፡ በየማነ፡ ተቅዋመ፡ ማኅቶት፡ ወአሐቲ፡ በፀጋማ፤

አንዲቱ፡ በቀኟ፤ አንዲቱ፡ በግራዋ፡ በቅሰው፡ በልጠዋት፡ ያያል፤ ይኸውም ምሳሌ፡ ነው፤ ተቅዋም፡ የእስራኤል፤ ዘይቱ፡ የረድኤት፤ መብራቱ፡ የተድላቸው፤ የደስታቸው፤ መክደኛው፡ የረድኤት፤ ፍጻሜው፡ ግን፤ ተቅዋም፡ የእመቤታችን፤ ወርቁ፡ የንጽሕናዋ፡ የቅድስናዋ፤ ምንባረ፡ ፈትል፡ የማኅፀኗ፤ መግጠሚያው፡ የድንግልናዋ፤ እሳት፡ የመለኮት፤ ፈትል፡ የትስብእት፤ ዘይት፡ የመንፈስ፡ ቅዱስ፤ ሰባት፡ ሰባቱ፡ ምንባረ፡ ፈትል፡ አርባ፡ ዘጠኝ፡ ይሆናል፤ ለጊዜው፡ የዘሩባቤል፡ የዘመነ፡ መንግሥቱ፡ አምሳል፤ ዘመነ፡ መንግሥቱ፡ አርባ፡ ዘጠኝ፡ ነውና፡ ፍጻሜው፡ ግን እመቤታችን፡ ጌታን ከወለደች፡ በኋላ፡ የኖረችው፡ ዘመን፡

www.ethiopianorthodox.org

ወክልዔቲ፡ አጥባት፡ ዘይሠውጣ፡ ወዘ
ያስተናሥኣ፡ መሣውረ፡ ዘወርቅ፡

ሁለቱም፡ ጡቶቿ፡ የወርቁን፡
መግጠሚያ፡ አንሥተው፡ ዘይ
ታቸውን፡ ያፈስሳሉ፤

፬፤ ወእምዝ፡ ተስእልክዎ፡ ለዝኩ፡
መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፣

ከዚህ፡ በኋላ፡ የሚናገረኝን፡
መልአክ፡ ጠየቅሁት፣

ወእቤሎ፡ ምንትኑ፡ ዝንቱ፡ እግዚኦ፣

አቤቱ፡ ይህ፡ ምንድነው፡ ብዬ፡
ጠየቅሁት፤

፭፤ ወይቤለኒ፡ ዝኩ፡ መልአክ፡
ዘይትናገረኒ፡ ኢተአምርኑ፡ ከመ፡ ምን
ትዝ፣

የሚናገረኝ፡ መልአክ፡ ይህ፡
ምንም፡ ምን፡ እንደሆነ፡ አታ
ውቅምን፡ አለኝ፤

ወእቤሎ፡ አልቦ፡ እግዚእየ፣

አዎን፡ ጌታዬ፡ አላውቅም፡
አልሁት፤

፮፤ ወይቤለኒ፡ ዝ፡ ውእቱ፡ ቃለ፡
እግዚአብሔር፡ ዘይቤሎ፡ ለዘሩባቤል፣

ለዘሩባቤል፡ የነገረው፡ የእግዚ
አብሔር፡ ቃል፡ ይህ ነው፡ አለኝ፤

አኮ፡ በኃይል፡ ዓቢይ፡ ወአኮ፡ በጽንዕ፡
ዘእንበለ፡ በመንፈስየ፡ ይቤ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

አሕዛብን፡ የምታጠፋ፡ በአንተ፡
ለም፣ በኔ፡ ሥልጣን፡ ነው፡
እንጂ፤ አንድም፡ ቤተ፡ መቅ
ደስን፡ የምትሠራ፡ በአንተ፡
ኃይል፡ በአንተ፡ ጽናት፡ አይደ
ለም፤ በኔ፡ ረድኤት፡ ነው፡
እንጂ፣ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግ
ዚአብሔር፡ እንዲህ አለ፤

፯፤ ምንትኑ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ቅድ
ሜከ፡ ደብር፡ ዓቢይ፡ ዘታነክር፣

ይህ፡ የምታደንቀው፡ የአሕዛብ፡
ጭፍራ፡ ምን፡ ቁም፡ ነገር፡
ነው፤ አንተ፡ አስወጥተህ፡ የምት
ሰደው፡ አይደለምን፤ አንድም፡
ይህ፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ መፍ
ረስ፡ ምን፡ ቁም፡ ነገር፡ ነው፤
አንተ፡ የምትሠራው፡ አይ
ደለምን፤

ወአመጽኣ፡ ለዕብነ፡ ርትዕ፣

ቤተ፡ መቅደስን፡ እንዲሠሯት፡
አደርጋለሁ፤

ወአዔርያ፣

ሕዝቡና፡ አሕዛቡ፡ ተካክለው፡
ይሠሯታል፤

ወአሤንያ፣

አከናውናታለሁ፤

ወአም[illegible]



፰፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡
ኀቤየ፣

ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ከኔ፡ ዘንድ፡
መጣ፡ ተነገረ፤

፱፤ ወይቤለኒ፡ ዕደው፡ ዘሩባቤል፡
ሣረራሁ፡ ለዝንቱ፡ ቤት፡ ወእደዊሁ፡
ይፌጽማሁ፣

ቤተ፡ መቅደስን፡ የዘሩባቤል፡
ወገኖች፡ ይጀምሩታል፣ እጆቹ
ይፈጽሙታል፤

ወተአምር፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡
ይመልክ፡ ፈነወኒ፡ ኀቤከ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡
ወደአንተ፡እንደላከኝ፡ታውቃለህ፤

፲፤ እስመ፡ ዘአስተኃቀረ፡ ለኅዳጥ፡
መዋዕል፡ ያስተሐቅር፣

ቤተ፡ መቅደስን፡ የናቀ፣ ያቀለለ፡
መናቁ፡ ማቃለሉ፡ ለጥቂት፡
ዘመን፡ ነው፤ አንድም፡ ቤተ፡
መቅደስን፡ የሚንቅን፡ ሰው፡
ሥላሴ፡ ይንቁታል፣ ያቃል
ሉታል፣

ወይትፌሥሑ፣

ደስ፡ ይላቸዋል፤

ወይሬእይዋ፡ ለዕብነ፡ ናዕክ ውስተ፡
እዴሁ፡ ለዘሩባቤል፣

ቤተ፡ መቅደስን፡ በዘሩባቤል፡
እጅ፡ ተሠርታ፡ ያይዋታል፣
ዕብነ፡ ናዕክ፡ አኂት፣ ሕዝቡና፡
[illegible] ሠር

ወእሙንቱ፡ ሰብእቱ፡ አዕይንቲሁ፡ ለእ
ግዚአብሔር፡ ውእቱ፡ ዘይኔጽር፡ ኵሎ፡
ምድረ፣

ሁሉን፡ የሚጠብቅ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ ዓይኖቹ፡ ሰባት፡ ናቸው፡
አለኝ፣ ትርጓሜው፡ እንዳለፈው፡
ነው፤

፲፩፤ ወእቤሎ፡ ምንትኑ፡ እንከ፡
እልክቱ፡ ክልዔቱ፡ አዕፁቀ፡ ዘይት፡
ዘየማነ፡ ተቅዋመ፡ ማኅቶት፡ ወዘፀጋማ፣

በተቅዋም፡ በቀኝ፡ በግራዋ፡ ያየ
ኋቸው፡ እኒህ፡ ሁለቱ፡ የዘይ
ቶች፡ ጫፎች፡ ምንድናቸው፡
አልሁት፤

፲፪፤ ወካዕበ፡ እቤሎ፡ ምንትኑ፡
አዕፁቀ፡ ዘይት፡ እሉ፡ ፪ቱ፡ ዘውስተ፡
እዴሁ፡ ወ፪ቱ፡ አጥባት፡ ዘይሠውጡ፡
ወዘያሥተናስእ፡ መሣውረ፡ ዘወርቅ፣

የወርቅ፡ የሆነ፡ መክደኛውን፡
እያነሣ፡ ሲያልባቸው፡ የማየው፡
እኒህ፡ ሁለቱ ጡቶች፡ ምንድ
ናቸው፡ አልሁት፤

፲፫፤ ወይቤለኒ፡ ኢተአምርኑ፡ ከመ፡
ምንት፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፣

ይህ፡ ምንም፡ እንደሆነ፡ አታ
ውቅምን፡ አለኝ፤

እቤሎ፡ አልቦ፡ እግዚእየ፣

ጌታዬ፡ አላውቅም፡ አልሁት፣

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ወይቤለኒ፡ እሉኬ፡ ደቂቀ፡ ጠላት፡ እሙንቱ፡ እለ፡ ይቀውሙ፡ ቅድመ፡ እግዚእ፡ ኵሉ፡ ምድር፤

ደቂቀ፡ ቅብዓት፡ ሲል፡ ነው፤ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ የሚቆሙ፡ ዮሴዕ፡ ዘሩባቤል፡ ናቸው፡ አለኝ፤ አንድም፡ የትንቢት፡ መገኛ፡ ነቢያት፡ የትምህርት፡ መገኛ፡ ሐዋርያት፡ ናቸው፡ አለኝ።

## ምዕራፍ ፭

### ጉባዔ

፩፤ ወካዕበ፡ ተመየጥኩ፤

ዳግመኛ፡ አንዱን፡ ነገር፡ ከማየት፡ አንዱን፡ ነገር፡ ወደማየት፡ ተመለስሁ፤

ወርኢኩ፡ ማዕፀደ፡ ዘይሠርር፤

ማጭድ፡ ሲወረወር፡ አየሁ፤

፪፤ ወይቤለኒ፡ ምንተ፡ ትሬኢ፤

ምን፡ ታያለህ፡ አለኝ፤

ወእቤሎ፡ ማዕፀደ፡ ዘይሠርር፤

የሚወረወር፡ ማጭድ፡ አየሁ፡ አልሁት፤ ክበደ፡ በቀል፡ ነው፤

ኑኁ፡ እሥራ፡ በእመት፤

አቈልቋዩ፡ ሀያ፡ ክንድ፡ ነው፡ አለ፤ በአሕዛብ፡ የሚመጣ፡ መከራ፡ ነው፤

ወስፍሑ፡ ዐሥር፡ በእመት፤

ወርዱ፡ ዐሥር፡ ክንድ፡ ነው፡ [illegible] በእስራኤል፡ የሚመጣ፡

፫፤ ወይቤለኒ፡ ዝንቱኬ፡ ዘየሐውር፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ ምድር፤

ይህ፡ በዓለሙ፡ ሁሉ፡ የሚመጣ፡ መከራ፡ ነው፡ አለኝ፤

ለኵሉ፡ ሰራቂ፡ ዝንቱ፡ ይትቤቀሎ፡ ወይቀትሎ፤

ሌባውን፡ ቀማኛውን፡ ተበቅሎ፡ ያጠፋዋል፤

ወለኵሉ፡ ዘይምሕል፡ በሐሰት፡ ዝንቱ፡ ይትቤቀሎ፡ በሞት፤

በሐሰት፡ የሚምለውን፡ ሁሉ፡ ይህ፡ ተበቅሎ፡ ያጠፋዋል፤

፬፤ ወአበውኦ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ቤተ ኵሉ፡ ዘይምሕል፡ በስምየ፡ በሐሰት፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በሐሰት፡ ስሜን፡ ጠርቶ፡ ወደሚምል፡ ሰው፡ ቤት፡ አመጣዋለሁ፡ አለ፤

ወየኅድር፡ ማዕከለ፡ ቤቱ፤

በወገኖቹ፡ መካከል፡ ያድራል፤

ወየሐልቅ፡ ዕፀዊሁ፡ ወዕበኒሁ፤

ብርቱውንም፡ ደካማውንም፡ ያጠፋል፤

፭፤ ወመጽአ፤ ዝኩ፡ መልአክ፡ ዘይትናገረኒ፤

የሚነግረ[illegible]



ወይቤለኒ፡ ነጽር፡ በአዕይንቲከ፤

አንገትህን፡ አቅንተህ፡ እይ፡ አለኝ፤

ወርኢ፡ መስፈርተ፡ ዘየሐውር፤

ወደ፡ ባቢሎን፡ የሚሄድ፡ ሚዛን፡ እይ፤

፮፤ ወእቤሎ፡ ምንትኑ፡ ዝንቱ፤

ይህ፡ ምንድነው፡ አልሁት፤

ወይቤለኒ፡ ዝንቱ፡ መሥፈርት፡ ዘየሐውር፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ ምድር፡ ዓመፃሆሙ፡ ውእቱ፤

በበደላቸው፡ ምክንያት፡ ወደ፡ ባቢሎን፡ የሚሄድ፡ ፍትሐ፡ እግዚአብሔር፡ ነው፡ አለኝ፤ ሚዛን፡ እንዳያዳላ፡ ፍትሐ፡ እግዚአብሔርም፡ አያዳላምና፤

፯፤ ወናሁ፡ መክሊተ፡ አረር፡ ይትነሣእ፤

እነሆ፡ አዋቂ፡ ይነሣል፡ ማለት፡ ፍትሐ፡ እግዚአብሔር፡ ይደረጋል፤

ወብእሲት፡ ትነብር፡ ማዕከለ፡ መስፈርት፤

ሴት፡ በሚዛኑ፡ መካከል፡ ተቀምጣለች፡ ማለት፡ ባቢሎን፡ በእግዚአብሔር፡ እጅ፡ ተይዛለች፤

፰፤ ወይቤለኒ፡ ዛቲ፡ ኃጢአት፤

ይችም፡ በኃጢአት፡ ምክንያት፡ ነው፡ አለኝ፤ አንድም፡ ኃጥ[illegible] ናት፡ አለኝ፤

ወወረውዋ፡ ማዕከለ፡ መስፈርት፤

በሚዛኑ፡ መካከል፡ አደረጓት፡ ማለት፡ በፍትሐ፡ እግዚአብሔር፡ ያዟት፡ ማለት፡ ነው፤

ወወረዉ፡ ዕብነ፡ አረር፡ ውስተ፡ አፉሃ፤

ደንጊያ፡ አጐረሷት፤ ለልማዱ፡ ሚዛን፡ በአንድ፡ ወገን፡ ያለው፡ ዘንበል፡ ሲል፡ ደንጊያ፡ ያጐርሱታል፤ እንደዚህም፡ ሁሉ፡ ሥላሴ፡ ኃጢአቷን፡ መርምረው፡ ፍዳዋን፡ ያመጡባታል፤

፱፤ ወአንሣእኩ፡ አዕይንትየ፤

አንገቴን፡ አቅንቼ፡ አየሁ፤

ወርኢኩ፡ ፪ቱ፡ አንስት፡ የሐውራ፤

ቂሮስ፡ ዳርዮስ፡ ወደባቢሎን፡ ሲሄዱ፡ አያለሁ፤

ወነፋስ፡ ውስተ፡ ክነፊሆን፤

በእጃቸው፡ በእግራቸው፡ ፍጥነት፡ አለ፡ ማለት፡ በሠራዊቶቻቸው፡ ሥልጣን፡ አለ፤

ወቦቶን፡ ክንፍ፡ ውስተ፡ እገሪሆን፤

በእግራቸው፡ ፍጥነት፡ አለ፡ ማለት፡ በተወራጆች፡ ሠራዊት፡ ሥልጣን፡ አለ፤

ወነሥኣሃ፡ ለዛቲ፡ መሥፈርት፡ ማዕከለ፡ ሰማይ፡ ወምድር፤

ሚዛኑን፡ በሰማይና፡ በምድር፡ መካከል፡ ይይዙታልና፡ በዚያ፡

www.ethiopianorthodox.org

ልማድ፡ ተናገረው፡ እንደዚ
ህም፡ ሁሉ፡ በጻድቃንና፡ በመ
ላእክት፡ ፊት፡ በፍዳ፡ ተይዛ፡
አየኋት፤

፲፤ ወእቤሎ፡ ለመልአክ፡ ዘይ
ትናገረኒ፤

የሚናገረኝን፡ መልአክ፡ እንዲህ፡
አልሁት፤

አይቴ፡ ይወስዳ፡ መስፈርተ፡ እላንቱ፡
አንስት፤

እኒህ፡ ሴቶች፡ ይህን፡ ሚዛን፡
ወዴት፡ ይወስዱታል፡ አልሁት፤

፲፩፤ ወይቤለኒ፡ የሐንፃ፡ ቤተ፡
በምድረ፡ ባቢሎን፤

በባቢሎን፡ ቤት፡ ይሠራሉ፡
አለኝ፤ አንድም፡ ይሕንፃ፡ ቤተ፤
በባቢሎን፡ የጥፋት፡ ቤት፡ ይሠሩ፡
ዘንድ፡ ይሄዳሉ፡ አለኝ፤

ወያስተዳልዋ፡ ወአንበራሃ፡ ህየ፡
አስተዳሊዎን፤

ሠርተው፡ አዘጋጅተው፡ ከዚያ፡
ያኖሯታል፡ ማለት፡ ኃጢአቷን፡
መዝነው፡ መርምረው፡ ጠሩን፡
እየከፈሉ፡ ሰደው፡ ያጠፏታል።

## ምዕራፍ ፮

፩፤ ወተመየጥኩ፡ አንሣእኩ፡
አዕይንትየ፤

ወርኢኩ፡ አርባዕተ፡ ሠረገላተ፡ እንዘ፡
የሐውሩ፡ ማዕከለ፡ ፪ቱ፡ አድባራት፤

አራቱ፡ ሊቃነ፡ መላእክት፡ በቂ
ሮስ፡ በዳርዮስ፡ አድረው፡
ሲመጡ፡ አየሁ፤

ወአድባሩኒ፡ ዘብርት፤

ተራሮቹ፡ ጽኑዓን፡ ናቸው፤

፪፤ ወውስተ፡ ሠረገላ፡ ቀዳማዊ፡
አፍራስ፡ ቀይሐን፤

በመጀመሪያው፡ ሠረገላ፡ የተ
ቀመጡ፡ የመጀመሪያውን፡ ሠረ
ገላ፡ የሚመሩ፡ የሚከተሉ፡
በሐመር፡ ፈረስ፡ የተቀመጡ፡
ናቸው፤ የባቢሎንን፡ ሰዎች፡
ደም፡ እናፈስሳለን፡ ሲሉ፡ በሐ
መር፡ ፈረስ፡ ተቀምጠው፡ ይታ
ዩታል፤

፫፤ ወውስተ፡ ካልዕ፡ ሠረገላ፡
አፍራስ፡ ጸሊማን፤

በሁለተኛው፡ ሠረገላ፡ የተቀ
መጡ፡ ሁለተኛውን፡ ሠረገላ፡
የሚመሩ፤ ሁለተኛውን፡ ሠረ
ገላ፡ የሚከተሉ፡ በዱሪ፡ ፈረስ፡
የተቀመጡ፡ ናቸው፤ በባቢሎን፡
ሰዎች፡ መከራ፡ እናመጣለን፡
ሲሉ፡ በዱሪ፡ ፈረስ፡ [illegible]



ወውስተ፡ ሠረገላ፡ ሣልስ፡ አፍራስ፡
ፀዓድው፤

በሦስተኛው፡ ሠረገላ፡ የተቀ
መጡ፡ ሦስተኛውን፡ ሠረገላ፡
የሚመሩ፡ የሚከተሉ፡ በአምባ
ላይ፡ ፈረስ፡ የተቀመጡ፡ ናቸው፤
ለእስራኤል፡ ተድላ፡ ደስታ፡
እናደርጋለን፡ ሲሉ፡ በአምባ
ላይ፡ ፈረስ፡ ተቀምጠው፡ ይታ
ዩታል፤

ወውስተ፡ ሠረገላ፡ ራብዕ፡ አፍራስ፡
ኰሳኵሳን፡ ወሐመዳውያን፤

በአራተኛው፡ ሠረገላ፡ የተቀ
መጡ፡ አራተኛውን፡ ሠረገላ፡
የሚመሩ፡ የሚከተሉ፡ በጥርኝ፡
ፈረስ፡ በቡላ፡ ፈረስ፡ የተቀ
መጡ፡ ናቸው፤ በጥርኝ፡ ፈረስ፡
የተቀመጡት፡ ሕዝቡና፡ አሕዛቡ፡
አንድ፡ ሁነው፡ ይወጣሉ፡ ሲሉ፤
በቡላ፡ ፈረስ፡ የተቀመጡት፡
ሕዝቡና፡ አሕዛቡ፡ ተጋብተው፡
የተዋለዱ፡ ናቸው፤

፬፤ ወእቤሎ፡ ለመልአክ፡ ዘይትና
ገረኒ፡ እግዚእየ፡ ምንትኑ፡ ዝንቱ፤

የሚናገረኝን፡ መልአኩን፡ ጌታዬ፡
ይህ፡ [illegible] አልሁት፤

፭፤ ወይቤለኒ፡ ዝኩ፡ መልአክ፡
ዘይትናገረኒ፡ እሉ፡ እሙንቱ፡ ነፋሳተ፡
ሰማይ፡ አርባዕቱ፡ እለ፡ ይቀውሙ፡
ቅድመ፡ እግዚአ፡ ኵሉ፡ ምድር፤

አገሩን፡ ሁሉ፡ በሚገዛ፡ በጌታ፡
ፊት፡ የሚቆሙ፡ አራቱ፡ ሊቃነ፡
መላእክት፡ ናቸው፡ አለኝ፤

፮፤ ወዘንበ፡ አፍራስ፡ ጸሊማን፡
የሐውሩ፡ ሰሜነ፤

በዱሪ፡ ፈረስ፡ የተቀመጡት፡
ወደባቢሎን፡ ይሄዳሉ፡ በባቢሎን፡
መከራ፡ እናመጣለን፡ ሲሉ፤

ወእሉ፡ አፍራስ፡ ፀዓድው፡ የሐውሩ፡
ድኅሬሆሙ፤

በአምባላይ፡ ፈረስ፡ የተቀመ
ጡትም፡ እስራኤልን፡ ደስ፡
ለማሰኘት፡ እነዚያን፡ ተከት
ለው፡ በኋላ፡ በኋላ፡ ይሄዳሉ፤

ወየሐውሩ፡ ቀይሐን፡ ምድረ፡ ሰሜን፤

በሐመር፡ ፈረስ፡ የተቀመጡትም፡
ወደባቢሎን፡ ይሄዳሉ፤

፯፤ ወኰሳኵሳን፡ ይወጽኡ፤

በጥርኝ፡ ፈረስ፡ የተቀመጡት፡
ወደባቢሎን፡ ይሄዳሉ፡ ማለት፡
ሕዝብና፡ አሕዛብ፡ አምነው፡
ይወጣሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይኄጽሩ፡ ወየሐውሩ፡ ይዑድዋ፡ ለምድር፤

አገሩን፡ ሁሉ፡ ይዞሩ፡ ዘንድ፡ ይሄዳሉ፤

ወያድዋ፡ ለምድር፤

ምድርን፡ ዞሯት፤

፰፤ ወከልሀ፡ ወይቤለኒ፤

ቃሉን፡ አሰምቶ፡ እንዲህ፡ አለኝ፤

ናሁ፡ እሉ፡ የሐውሩ፡ ምድረ፡ ሰሜን፡ ያዕርፍዋ፡ ለመዓትየ፡ በምድረ፡ ሰሜን፤

ቁጣዬን፡ በባቢሎን፡ ያሳርፏት፡ ዘንድ፡ ወደባቢሎን፡ ይሄዳሉ፤

፱፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀቤየ፤

ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ መጣ፡ ተነገረ፤

፲፤ ወይቤለኒ፡ ንሣእ፡ እምዔዋ፡ በኀበ፡ መላእክት፤

ከአለቆች፡ ዘንድ፡ ሂደህ፡ ከተማረኩት፡ ልጆች፡ ተቀበል፡ አለኝ፤

ወበኀበ፡ በቋዕያኒሃ፤

ሕግን፡ ከሚረቧት፡ ከሚጠቅሟት፤

ወበኀበ፡ እለ፡ የአምርዋ፤

ሕግን፡ ከሚወዷት፡ ሄደህ፡ ተቀበል፤

ወትበውእ፡ አንተ፡ ይእተ፡ አሚረ፡ ቤተ፡ ኢዮስያስ፡ ወልደ፡ ሶፎንያ፡ ዘመጽአ፡ እምባቢሎን፤

አንተ፡ ያን፡ ጊዜ፡ ከባቢሎን፡ ከመጣ፡ ከሶፎንያ፡ ልጅ፡ ከኢዮስያስ፡ ቤት፡ ግባ፤

፲፩፤ ወትነሥእ፡ ወርቀ፡ ወብሩረ፤

ወርቁን፡ ብሩን፡ ተቀበል፤

ወትገብሮ፡ አክሊላተ፤

አክሊሉን፡ ሥራ፤

ወታስተቄጽሎ፡ ለዮሴዕ፡ ወልደ፡ ዮሴዴቅ፡ ካህን፡ ዓቢይ፤

ለዮሴዴቅ፡ ልጅ፡ ለደጉ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ለዮሴዕ፡ ድፋለት፤

፲፪፤ ወበሎ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ በለው፤

ወናሁ፡ ብእሲ፡ ሠረቃዊ፡ ሠርፀ፡ መንግሥት፡ ስሙ፤

የዘሩባቤል፡ ስሙ፡ ዘወጽአ፡ እምባቢሎን፡ ዘሠረፀ፡ እመንግሥት፡ ይባላል፤

ወይሠርፅ፡ እምታሕቴሁ፤

ከዮሴዕ፡ በታች፡ ይነግሣል፤

፲፫፤ ወየሐንፅ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፤

ቤተ፡ መቅደስ[illegible]



ወውእቱ፡ ይነሥእ፡ ትርሲቶ፤

እሱ፡ ጌጡን፡ ሁሉ፡ ይቀበላል፤

ወይነብር፡ ዲበ፡ መንበሩ፡ ወይኴንን፤

በዙፋኑ፡ ተቀምጦ፡ ይፈርዳል፤

ወካህን፡ ይነብር፡ በየማኑ፤

ሊቀ፡ ካህናቱ፡ በቀኙ፡ ይቀመጣል፤

ምክር፡ ወሰላም፡ ማዕከለ፡ ፪ሆሙ፤

በንጉሡና፡ በሊቀ፡ ካህናቱ፡ መካከል፡ ምክር፡ ፍቅር፡ አንድነት፡ ጸንቶ፡ ይኖራል፤ አንድም፡ ምግባር፡ ሃይማኖት፤

፲፬፤ ወአክሊልሰ፡ ለእለ፡ ይትኤገሥዎ፤

አክሊሉም፡ መከራውን፡ ለሚታገሡ፤

ወለበቋዕያኒሃ፤

ሕግን፡ ለሚረቧት፡ ለሚጠቅሟት፤

ወለእለ፡ የአምርዋ፤

ሕግን፡ ለሚወዷት፡ ለነቢያት፡ ለካህናት፡ ነው፤ አንድም፡ ደገኛው፡ አክሊል፡ ግን፡ መከራውን፡ ለሚታገሡ፡ ሕግን፡ ለሚረቧት፡ ለሚወዷት፡ ለሰማዕታት፡ ለሐዋርያት፡ ነው፤

ወለትርሲቶሙ፡ ለደቂቀ፡ ሶፎንያ፡ መዘምራን፡ ውስተ፡ ቤተ እግዚአብሔር፤

ጥቃቅኑም፡ አክሊል፡ ቤተ፡ እግ[illegible]ለሰ[illegible]

፲፭፤ ወይመጽኡ፡ እለሂ፡ እምርኁቃን፡ እምኔሆሙ፤

ከሳቸው፡ የራቁ፡ አሕዛብም፡ በሚጠት፡ አምነው፡ ይመጣሉ፤

ወየሐንፁ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፤

ቤተ፡ መቅደስን፡ ይሠራሉ፤

ወተአምሩ፡ ከመ፡ ፈነወኒ፡ ኀቤክሙ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ወደእናንተ፡ እንደላከኝ፡ ታውቃላችሁ፤

ወእመሰ፡ ሰሚዓ፡ ትሰምዑ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክነ፤

የፈጣሪያችሁን፡ ቃል፡ ብትሰሙ፡ ይህ፡ ይደረግላችኋል።

## ምዕራፍ ፯

፩፤ ወእምዝ፡ በራብዕት፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለዳርዮስ፡ ንጉሥ፤

ከዚህም፡ በኋላ፡ ዳርዮስ፡ በነገሠ፡ በአራተኛ፡ ዘመን፤

ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ዘካርያስ፡ አመ፡ ረቡዑ፡ ለሠርቀ፡ ታስዕ፡ ወርኅ፤

በዘጠነኛ፡ ወር፡ ታኅሣሥ፡ በገባ፡ በአራተኛ፡ ቀን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወወርኅ፡ ወርኃ፡ ካሌል፣

ወርኑም፡ ታኅሣሥ፡ ነው፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ወደዘካርያስ፡ መጣ፡ ተነገረ፤

፪፤ ወፈነዎሙ፡ ንጉሥ፡ እምቤቴል፡ ኀበ፡ እስራኤል፡ ለአሴር፡ ወለአኔሴር፡ ወለቤተ፡ አል፡ ወለሰብዑ፣

ንጉሥ፡ ከቤቴል፡ ወደ፡ እስራኤል፡ አሴርን፣ አኔሴርን፣ ቤተ፡ አልን፣ ሰዎቹን ላከ፤ አንድም፡ ሰብዑ፡ ስም፡ ነው፤ ሰብዑን፡ ላከ፤

ከመ፡ ይስአሉ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ካህናት፡ ዘውስተ፡ ቤተ እግዚአብሔር፣

ቤተ፡ መቅደስን፡ ከሚያገለግሉ፡ ካህናቱ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ይጠይቁ፡ ዘንድ፡ ላካቸው፤

፫፤ ወይቤልዎሙ፡ ለካህናት፡ እለ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ እግዚአብ ሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ፡ ወለነቢያት፣

ነቢያት፡ ካህናትን፡ እንዲህ፡ አሏቸው፤

ንብኪኑ፣

ንጹምኑ፡ ሲል ነው፤

በሐሙስ፡ ወርኅ፡ በከመ፡ ገበርነ፡ እምጕንዱይ፡ ዓመት፣

ከሰባ፡ ዘመን፡ ጀምሮ፡ እንደ ጾምን፡ በአምስተኛው፡ ወር፡ በነሐሴ፡ እንጹምን፤ አንድም፡ ቦአኑ፡ ዝየ፡ ዘቅድሳት፡ የሚል፡ ይገኛል፣ ንዋየ፡ ቅድሳቱ፡ ገባን፡ ላኪው፡ ዳርዮስ፡ ነው፣ የዚህ፡ መልሱ፡ አልመጣም፣ በዚህ፡ ጊዜ፡ የተላኩ፡ ኤሬጋል፡ ሴር ያጼር፡ እረብማግ፡ መንገናሶር፡ ሰማንት፡ ናቸው፣ ከሰባ፡ ዘመን ከመጀመሪያው፡ ጀምሮ፡ እንደ፡ ጾምን፡ ባምስተኛው፡ ወር፡ በነሐሴ፡ እንጹምን፤

፬፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀቤየ፣

ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ወደኔ መጣ፡ ተነገረ፤

፭፤ ወይቤለኒ፡ በሎሙ፡ ለሕዝብ፡ ወለካህናት፣

ሕዝቡንም፡ ካህናቱንም፡ እንዲህ፡ በላቸው፡ አለኝ፤

ቦኑ፡ ዘጾምክሙ፡ ጾመ፡ ረቡዕ፡ ወጾመ፡ ሐሙስ፣

በውኑ፡ የጾማችሁት፡ አለ? የሐምሌን፡ ጾም፣ የነሐሴን፡ ጾም፤

ወጾመ፡ ሰቡዕ፣

የጥቅምትን፡ ጾም፤

ወጾመ፡ አሥር፣

የጥርን፡ ጾም፤



እምሰብዓ፡ ዓም፣

ከሰባ፡ ዘመን፡ ጀምሮ፡ የጾማችሁት፡ ጾም፡ አለ?

፮፡ ቦኑ፡ ጾመ፡ ዘጾምክሙ፡ ሊተ፡ ወእመሂ፡ በላዕክሙ፡ ወሰተይክሙ፡ አኮኑ፡ ሰርእስክሙ፡ ትበልዑ፡ ወትሰትዩ፣

በውኑ፡ ለኔ፡ ብላችሁ፡ የጾማችሁት፡ ጾም፡ አለን፣ ብትበሉስ፡ ብትጠጡስ፡ ለራሳችሁ፡ ብላችሁ፡ የምትበሉ፡ የምትጠጡ፡ አይደለምን፤

፯፤ አኮኑ፡ ዝንቱ፡ ነገሩ፡ ዘነበበ፡ እግዚአብሔር፡ በአፈ፡ ነቢያቲሁ፡ ቀደምት፣

በቀደሙ፡ ነቢያት፡ ቃል፡ እግዚአብሔር፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ አይደለምን፤

አመ፡ ትነብር፡ ኢየሩሳሌም፡ ወትትፌሣሕ፣

ኢየሩሳሌም፡ ጠላት፡ ጠፍቶላት፡ ደስ፡ ብሏት፡ ትኖር፡ በነበረ፡ ጊዜ፤

ወአህጉሪሃኒ፣

ጥቃቅኑ፡ አህጉር፤

ወአድያሚሃኒ፣

[illegible]

ወአሕቃላቲሃኒ፣

አውራጃዋ፤

ወበሐውርቲሃኒ፡ ንቡራን፣

አገሮቿ፡ ሁሉ፡ ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ ይኖሩ፡ በነበረ፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ አይደለምን፤

፰፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ዘካርያስ፣

ከዘካርያስ፡ ዘንድ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ መጣ፡ ተነገረ፤

፱፤ ወይቤሎ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ አለው፤

ኰንኔ፡ ጽድቅ፡ ኰንኑ፣

እውነት፡ ፍርድን፡ ፍረዱ፤

ወግበሩ፡ ምጽዋተ፣

ምጽዋትን፡ መጽውቱ፤

ወምሕረተ፡ ላዕለ፡ ቢጽክሙ፡ ኵልክሙ፣

ሁላችሁም፡ ባልንጀሮቻችሁን፡ ይቅር፡ በሉ፤

፲፤ ዕቤረ፡ ወዕጓለ፡ ማውታ፣

ባልቴቲቱን፣ አባት፡ እናቱ፡ ጥለውት፡ የሞቱትን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወፈላሴ፡ ወነዳየ፡ ኢትትአገሉ፣

መጻተኛውን፡ ድኃውን፡ አትቀሙ፤

ወኢትትቀየሙ፡ ቢጸክሙ፣

ባልንጀሮቻችሁን፡ አትቀየሙ፤

ወኢትፁሩ፡ ሎሙ፡ እኩየ፣

በቀልን፡ አታድርጉባቸው፤

፲፩፤ ወአበዩ፡ አጽምዖ፣

መስማቱን፡ እምቢ፡ አሉ፤

ወሜጡ፡ ዘባናሙ፣

ዘባነ፡ ልቡናቸውን፡ ወደከፉ፡ ነገር፡ መለሱ፤

ወአስተሐቀሩ፣

ሕጉን፡ ናቁ፡ አቃለሉ፤

ወሜጡ፡ እዝኖሙ፡ ከመ፡ ኢይስምዑ፣

እንዳይሰሙ፡ ጆሯቸውን፡ ከመስማት፡ መለሱ፤

፲፪፤ ወአክሃዱ፡ ልቦሙ፡ ወአዕለዉ፣

ልቡናቸውን፡ አስካዱ፤

ከመ፡ ኢይስምዑ፡ ቃለ፡ ዘለአከ፡ ኀቤሆሙ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ዘመንፈሱ፡ በእደ፡ ነቢያት፡ ቀደምት፣

መንፈስ፡ ቅዱስን፡ መምህር፡ በማድረግ፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በነቢያት፡ ቃል፡ ያናገረውን፡ ነገር፡ እንዳይሰሙ፡ ጆሮዋቸውን፡ መለሱ፤

ወኮነ፡ ዓቢየ፡ መዓተ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብሔር፡ መዓቱ፡ ጽኑ፡ ነው፤

፲፫፤ ወበከመ፡ ይቤሎሙ፡ ዓበዩ፡ ሰሚዓ፣

እሱ፡ እንደ፡ ነገራቸው፡ መስማቱን፡ እምቢ፡ እንዳሉ፤

ከማሁ፡ ይኬልሁ፡ ወኢይሰምዖሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

አሁን፡ እንደተናገርሁት፡ በመከራ፡ ተይዘው፡ ይጮሃሉ፣

ሁሉን የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ አይሰማቸውም፤

፲፬፤ ወእዘርዎሙ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፡ ዘኢየአምሩ፣

ወደማያውቋቸው፡ ወደ፡ አሕዛብ፡ ሁሉ፡ እበትናቸዋለሁ፣

ወትማስን፡ ምድሮሙ፡ በድኅሬሆሙ፡ በሐሪት፡ ወበግብአት፣

እስራኤል፡ ከተማረኩ፡ በኋላ፡ ኢየሩሳሌምን፡ አሕዛብ፡ ተመላልሰው፡ ያጠፏታል፣

ወአረስያ፡ ሙስንተ፡ ለምድር፡ ኅሪት፣

እንተ፡ ታውኅዝ፡ ሀሊበ፡ የሚላት፡ ኢየሩሳሌምን፡ የተፈታች፡ አደርጋታለሁ፡



# ምዕራፍ ፰

፩፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀቤየ፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ወደኔ፡ መጣ፡ ተነገረ፤

፪፤ ወይቤ፡ ከመዝ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ቀናዕኩ፡ ላዕለ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወላዕለ፡ ጽዮን፡ ዓቢየ፡ ቅንዓተ፣

በኢየሩሳሌምና፡ በጽዮን፡ ላይ፡ ፈጽሜ፡ ቀናሁ፤

ወተማዕኩ፡ ዓቢየ፡ መዓተ፣

በአሕዛብ፡ ላይ፡ ፈጽሜ፡ ተቆጣሁ፤

፫፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

እትመየጣ፡ ለጽዮን፣

ጽዮንን፡ ከመዓት፡ ወደምሕረት፡ እመለስላታለሁ፤

ወአኃድር፡ በማዕከላ፡ ለኢየሩሳሌም፣

በኢየሩሳሌም፡ መካከል፡ በረድ

ሌት፡ [illegible]

ወትሰመይ፡ ኢየሩሳሌም፡ ሀገረ፡ ጽድቅ፣

ኢየሩሳሌም፡ ምግባር፡ ትሩፋት፡ የሚሠራባት፡ አሠርቱ፡ ቃላት፡ የሚነገሩባት፡ አገር፡ ትባላለች፤

ወደብረ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብሔር፡ መዲና፡ ትባላለች፤

ወደብረ፡ መቅደሱ፣

የመመስገኛው፡ ቦታ፡ ትባላለች፤

፬፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ አለ፤

ወዓዲ፡ ይነብሩ፡ አዕሩግ፡ ወሊቃውንት፡ ውስተ፡ መርህባ፡ ለኢየሩሳሌም፣

ዓዲ፡ ለዜዋዌ፡ ነው፤ አንድም፡ ለዳዊት፣ ለሰሎሞን፣ ዳግመኛ፡ ሽማግሎች፡ ሊቃውንቱ፡ በኢየሩሳሌም፡ አደባባይ፡ ይቀመጣሉ፤ አንድም፡ በዘመነ፡ሐዲስ፡ ሽማግሎች፡ ሊቃውንቱ፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ አደባባይ፡ ይቀመጣሉ፤

ወለኵሎሙ፡ ምርጉዞሙ፡ ውስተ፡ እደዊሆሙ፣

ሁሉም፡ ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ እስኪያረጁ፡ ድረስ፡ አርፈው፡

www.ethiopianorthodox.org

ይኖራሉ፤ አንድም፡ ሁሉም፡ በእጃቸው፡ መስቀል፡ አለ፤

፭፤ ወይመልዕ፡ መርህበ፡ ሀገር፡ ደቀ፡ ወአዋልደ፡ እለ፡ ይትዋነዩ፣

በኢየሩሳሌም፡ አደባባይ፡ ሕገ፡ ኦሪትን፡ የሚጨዋወቱ፡ ሴቶችን፡ ወንዶችን፡ ልጆች፡ ይመላል፤ አንድም፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ አደባባይ፡ ሕገ፡ ወንጌልን፡ የሚ ጨዋወቱ፡ ሐዋርያትን፡ አርድ ዕትን፡ ቅዱሳት፡ አንስትን፡ ይመላል፤

፮፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ለእመ፡ ተስእኖሙ፡ ለሕዝብየ፡ እለ፡ ተርፉ፡ ገዐ፡ ኵሉ፣ በቅድሜየ፡ ይሰዓን፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፣ አሥሩ፡ ነገድ፣ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀሩ፡ ትሩፋን፡ አምልኮት፡ ማብዛት፡ ቢሳናቸው፡ መራዳት ማብዛት፡ እኔን፡ ይሳነኛል? አንድም፡ ከባ ቢሎን፡ መውጣት፡ የተሳናቸው፡ እኔን ቢሳነኝ፡ ነዋ፤ አንድም፡ እነዚያን፡ ቢሳናቸው፡ በውኑ፡ እኔን፡ ይሳነኛል? አለ፡ እግዚ አብሔር፤

፯፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ናሁ፡ አነ፡ አድኅኖሙ፡ ለሕዝብየ፡ እም ብሔረ፡ ጽባሕ፣

እኔ፡ ወገኖቼ፡ እስራኤልን፡ ከፋ ርስ፡ አወጣቸዋለሁ፤

ወእምብሔረ፡ ዓረብ፣

ከግብጽ፡ አወጣቸዋለሁ፤

፰፤ ወእወስዶሙ፡ ወአኀድሮሙ፡ በማዕከለ፡ ኢየሩሳሌም፣

ወስጄ፡ በኢየሩሳሌም፡ መካከል፡ አኖራቸዋለሁ፤

ወበህየ፡ ይከውኑኒ፡ ሕዝብየ፣

በኢየሩሳሌም፡ ወገኖቼ፡ ይሆናሉ፤

ወአነሂ፡ እከውኖሙ፡ አምላኮሙ፡ በጽ ድቅ፡ ወበርትዕ፣

በኢታምልክ፡ በዘጠኙ፡ ሕግ ጋት፡ ጸንተው፡ ቢኖሩ፡ እኔም፡ አድናቸዋለሁ፤

፱፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤



ይጸንዓ፡ እደዊሆሙ፡ ለእለ፡ ይሰምዑ፡ በእላንቱ፡ መዋዕል፡ ዘንተ፡ ነገረ፡ እም አፈ፡ ነቢያት፡ ቀደምት፣

በሚጠት፡ ከቀደሙ፡ ነቢያት፡ ይህን፡ ነገር፡ የሰሙ፡ ሰዎች፡ እጃቸው፡ ለመወርወር፡ ቃላ ቸው፣ ለመምከር፡ ይጸናል፤

እምአመ፡ ሣረሩ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ማደሪያ፡ ቤተ፡ መቅ ደስን፡ ከሠሩ፡ ጀምሮ፤

ወእምከመ፡ ተሐንፀ፡ ቤተ፡ እግዚ አብሔር፣

ቤተ፡ መቅደስም፡ ከመሠራቱ፡ አስቀድሞ፤ አንድም፡ ቤተ፡ ክር ስቲያን፡ ከመሠራቷ፡ አስቀድሞ፣

፲፤ እምቅድመ፡ እላንቱ፡ መዋዕል፣

ዝብጥ፡ ፪ተ፡ አዕማደ፡ ጽጌያት፡ ካለው፡ አስቀድሞ፤

ሰብእኒ፡ ኢረከበ፡ አስቦ፣

እስራኤል፡ ረድኤቱን፡ አላገኙም፤

ወእንስሳኒ፡ ኢረከበ፡ አስቦ፣

እንስሳትም፡ ገለባውን፡ ጭዱን፡ አላገኙም፤ አንድም፡ መምህራን፡ ዋጋቸውን፡ አላገኙም፣ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ትምህርቱን፡ አላገኙም፤

ወኢየአርፍ፡ ዘይበውእኒ፡ ወዘይወጽ እኒ፡ እምሕማም፣

ከአባር፡ የተነሣ፡ ዝናም፡ ለዘር፣ ጠል፡ ለመከር፡ ይሰጥ፡ እንደ ሆነ፡ ለማየት፡ የሚወጣው፡ የሚገባው፡ አያርፍም፤ አንድም፡ በተፈጥሮ፡ ወደዚህ፡ ዓለም የሚመጣው፡ በሞት፡ የሚሄ ደው፡ አያርፍም፡ ሲሞት፡ ሲተካ፡ ይኖራል፤

ወእፌኑ፡ ኵሎ፡ ሰብአ፡ ወእስተቃ ትል፡ በበይናቲሆሙ፡ ላዕለ፡ ቢጾሙ፣

ኅግ፡ ማኅግን፡ ሰድጄ፡ ባልንጀ ሮቻቸው፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ እንዲዋጉ፡ አደርጋቸዋለሁ፤

፲፩፤ ወይእዜኒ፡ አኮ፡ ከመ፡ ቀዲሙ፡ ዘእገብር፡ አነ፡ ላዕለ፡ እለ፡ ተርፉ፡ ሕዝብየ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፣ አሥሩ፡ ነገድ፣ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ በቀሩ፡ ወገኖች፡ ላይ፡ እንደ፡ ቀደሙ፡ እንደ፡ አባቶቻቸው፡ የማደርግ ባቸው፡ አይደለም፤

፲፪፤ ዳዕሙ፡ አርኢ፡ ሰላመ፣

ፍቅር፡ አንድነትን፡ እገልጣ ለሁ፡ እንጂ፤

ወወይንኒ፡ ይሁብ፡ ፍሬሁ፤

ወይኑም፡ ፍሬውን፡ ይሰጣል፣ እስራኤልም፡ አምልኮትን፡ ያቀርባሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

ምድርኒ፡ ትሁብ፡ ማዕረራ፤

ምድርም፡ የዘሩባትን፡ ታበቅላ
ለች፤ የተከሉባትን፡ ታጸድቃለች፤

ወሰማይኒ፡ ትሁብ፡ ዝናመ፤

ሰማይም፡ ዝናም፡ ለዘር፡ ጠል፡
ለመከር ትሰጣለች፤ አንድም፡
ሕዝቡ፤ አሕዛቡ፡ ምግባር፡ ሃይ
ማኖትን፡ ያቀርባሉ፤ አንድም፡
ነቢያት፡ ሐዋርያት፡ ትምህርትን፡
ያስተምራሉ፤

ወአወርሶሙ፡ ለእለ፡ ተርፉ፡ ሕዝብየ፡
ዘንተ፡ ኵሎ፤

ይህን፡ ሁሉ፡ አባቶች፡ አልቀው፡
ለቀሩ፡ ልጆች፡ እሰጣለሁ፤

፲፫፤ ወበከመ፡ ኮንክሙ፡ መርገመ፡
ወውጉዳነ፡ በውስተ፡ አሕዛብ፡ ቤተ፡
እስራኤል፡ ወቤተ፡ ይሁዳ፤

አሥሩ፡ ነገድ፤ ሁለቱ፡ ነገድ፡
በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ተሰ
ደባችሁ፡ እንደ፡ አነሣችሁ፡
አትቀሩም፤

ከማሁ፡ አድኅነክሙ፤

አድናችኋለሁ፤

ወትከውኑኒ፡ ለበረከት፤

ለበረከት፡ ትሆናላችሁ፤

ወአጥብዑ፡ ወአጽንዑ፡ እደዊክሙ፤

እጃችሁን፡ ለመወርወር፤ ቃላ
ችሁን፡ ለመምከር፡ አጽኑ፤

፲፬፤ እስመ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚ
አብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡ ብሏልና፤

ወበከመ፡ መሐልኩ፡ አሕስሞ፡ አሕ
ስም፡ ላዕሌክሙ፡ በዘአምዕዑኒ፡ አበዊ
ክሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡
ይመልክ፡ ወኢነሳሕኩ፤

አባቶቻችሁ፡ ባሳዘኑኝ፡ ገንዘብ፡
ቀድሞ፡ በናንተ፡ ላይ፡ ክፉ
ውን፡ ነገር፡ አደርግባቸው፡
ዘንድ፡ እንደማልሁ፡ በዚያው፡
እንዳልተመለስሁ፤

፲፭፤ ከማሁ፡ መከርኩ፡ ወሐለይኩ፡
በእማንቱ፡ መዋዕል፡ ከመ፡ እግበር፡
ሠናየ፡ ለኢየሩሳሌም፡ ወለቤተ፡ ይሁዳ፤

ዛሬም፡ በሚጠት፡ ለአሥሩ፡
ነገድ፡ ለሁለቱ፡ ነገድ፡ በጎ፡
ነገር፡ ረድኤትን፡ ትምህርትን፡
እሰጣቸው፡ ዘንድ፡ መከርኩ፤
ከዚያም፡ አልመለስም፤

ተአመኑ፡ እንከ፡ ከመ፡ ይከውን፡
ዝንቱ፡ ነገር፤

ይህ፡ ሚጠት፡ እንዲደረግ፡
እመኑ፤

፲፮፤ ወተናገሩ፡ ጽድቀ፡ ምስለ፡
ኵሉ፡ ሰብእ፡ ወምስለ፡ ቢጽክሙ፤

ከሰው፡ ሁሉ፡ ጋራ፤ ከባልንጀ
ሮቻችሁም፡ ጋራ፡ ሕግን፡
ተጨዋወቱ፤



ወኵነኔ፡ ሰላም፡ ኰንኑ፡ በውስተ፡
አናቅጺክሙ፤

በአደባባዮችሁም፡ የቀና፡ ፍርድ፡
ፍረዱ፤

፲፯፤ ወኵልክሙ፡ ኢትፁሩ፡ እኩየ፡
በልብክሙ፡ ለቢጽክሙ፤

ሁላችሁም፡ ባልንጀሮቻችሁን፡
ለመበቀል፡ በልቡናችሁ፡ ቂም፡
አታሳድሩ፤

ወኢታፍቅሩ፡ እንከ፡ ምሒለ፡ መሐላ፡
በሐሰት፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ በሐሰት፡
መማልን፡ አትውደዱ፤

እስመ፡ ዘንተ፡ ኵሎ፡ ጸላዕኩ፡ ይቤ፡
እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡
ይህን፡ ሁሉ፡ ጠላሁ፡ ብሏልና፤

፲፰፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡
ኀቤየ፤

ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ከእኔ፡
ዘንድ፡ መጣ፡ ተነገረ፤

፲፱፤ ወይቤለኒ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚ
አብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ
ሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ አለኝ፤

ጾመ፡ ረቡዕ፤

የሐምሌ፡ ጾም፤

ወጾመ፡ ሐሙስ፤

የነሐሴ፡ ጾም፤

ወጾመ፡ ሰብዑ፤

የጥቅምት፡ ጾም፤

ወጾመ፡ አሥር፤

የጥር፡ ጾም፤

ይኩን፡ ለቤተ፡ ይሁዳ፡ ለፍሥሓ፡
ወለሐሤት፤

ለነገደ፡ ይሁዳ፡ ተድላ፡ ደስታ፡
ይሁናቸው፤

ወለበዓላት፡ ሠናያት፤

በዓለ፡ ሠዊትን፤ በዓለ፡ መጸለ
ትን፡ ለማክበር፡ ይሁናችሁ፤

ወትትፌሥሑ፤

ደስ፡ ይበላችሁ፤

ወአፍቅሩ፡ ጽድቀ፡ ወሰላመ፤

በጎ፡ ነገርን፤ ፍቅር፡ አንድነ
ትን ውደዱ፤

፳፤ ናሁ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

እነሆ፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚ
አብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ዓዲ፡ ይመጽኡ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ ይነ
ብሩ፡ ውስተ፡ ብዙኅ፡ አህጉር፤

በየሀገሩ፡ የሚኖሩ፡ አሕዛብ፡
በሚጠት፡ ይመጣሉ፤ አንድም፡
በዘመነ፡ ሐዲስ፡ ይመጣሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፤ ወይትጋብዑ፡ ውስተ፡ አሐቲ፡ ሀገር፤

በኢየሩሳሌም፡ ይሰበሰባሉ፤

ወይብሉ፡ ንዑ፡ ንሑር፡ ወንትጋነይ፡ ለገጸ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኩሉ፡ ይመልክ፤

ከመሄዳቸው፡ አስቀድመው፡ ገጸ፡ ረድኤቱን፡ ለማግኘት፡ ሁሉን፡ ወደሚገዛ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ኑ፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤

ወንኅሥሥ፡ ገጸ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኩሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብ ሔርን፡ ገጸ፡ ረድኤቱን፡ እንሻ፤

ወይቤሉ፡ አሐዱ፡ ለካልዑ፤

ከአሕዛብ፡ አንዱ፡ አንዱን፡ በሚ ጠት፡ እንዲህ፡ ይለዋል፤

ተሐውርኑ፡ አንተ፤

አንተ፡ ወደኢየሩሳሌም፡ ልትሄድ፡ ትወዳለህ?

ወይብሎ፡ እወ፤

አወን፡ እሄዳለሁ፡ ይለዋል፤

ወአነኒ፡ አሐውር፤

እኔም፡ እሄዳለሁ፡ ይለዋል፤

፳፪፤ ወይመጽኡ፡ ብዙኃን፡ አሕዛብ፡ እንዘ፡ የኃሥሡ፡ ገጸ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኩሉ፡ ይመልክ፡ በኢየሩሳሌም፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብ ሔርን፡ ገጸ፡ ረድኤቱን፡ ሲፈልጉ፡ ብዙ፡ አሕዛብ፡ ወደኢየሩሳሌም፡ ይመጣሉ፤

ወይትመሐለሉ፡ ለገጸ፡ እግዚአብሔር፤

ገጸ፡ ረድኤቱን፡ ለማግኘት፡ ይለምናሉ፤

፳፫፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኩሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ይእተ፡ አሚረ፡ ይእኅዙ፡ አሠርቱ፡ ዕደው፡ ዘእምኩሉ፡ በሐውርተ፡ አሕ ዛብ፡ ጽንፈ፡ ልብሱ፡ ለብእሲ፡ አይ ሁዳዊ፤

ያንጊዜ፡ በሚጠት፡ ከአሕዛብ፡ አገር፡ የመጡ፡ አሥር፡ ሰዎች፡ ያንድ፡ የአይሁዳዊን፡ ልብስ፡ ይይዛሉ፤

ወይብልዎ፡ ነሐውር፡ ምስሌከ፡ እስመ፡ ሰማዕነ፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ሀሎ፡ ምስሌከ፤

ከአንተ፡ ጋራ፡ እንሄዳለን፡ ይሉ ታል፤ እግዚአብሔር፡ በረድኤት፡ ከአንተ ጋራ፡ እንዳለ፡ ሰምተና ልና፤ አንድም፡ በዘመነ፡ ሐዲስ፡ ከአሕዛብ፡ አገር፡ የመጡ፡ አሥር፡ ሰዎች፡ የአንድ፡ የአይሁዳዊን፡ ልብስ፡ ይይዛሉ፤ ከአንተ ጋራ፡ እንሄዳለን፡ ይላሉ፤ እግዚአብ ሔር፡ ከአንተ፡ ጋራ እንዳለ፡ ሰምተናል፡



## ምዕራፍ ፱

### ጉባዔ

፩፤ ተረፈ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ በምድረ፡ሲድራ፡ ወደማስቆ፤

እግዚአብሔር፡ በእስራኤል፡ ከሚ ናገረው፡ ነገር፡ የቀረ፡ በአሕ ዛብ፡ ያናገረው፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ በአሕዛብ፡ ያናገረው፡ ብዙ፡ ነገሩ፡ ይህ፡ ነው፤ ሲድራ፡ ያላት፡ ሶርያ፡ ናት፤ ደማስቆ፡ ከተማይቱ፡ ናት፤

መሥዋዕቱ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዓይኑ፡ ኩሉ፡ ሰብእ፡ ወኩሉ፡ ሕዝበ፡ እስ ራኤል፤

እግዚአብሔርንስ፡ መሥዋዕት፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡ የሚያ ሰኘው፡ የእስራኤል፡ የአሕዛብ፡ ዓይን፡ በሞት፡ ቢፈስ፡ ነው፤ አንድም፡ እስራኤልን፡ ደስ፡ የሚ ያሰኘው፡ የአሕዛብ፡ ዓይን፡ በሞት፡ ቢፈስ፡ ነው፤

፪፤ ወአንትሙሂ፡ በውስተ፡ ደወለ፡ ጢሮስ፡ ወሲዶና፤

በጢሮስ፡ በሲዶና፡ የምትኖሩ፡ የናንተም፡ ዓይን፡ በሞት፡ ቢፈስ፡ ነው፤

እስመ፡ ሐለዩ፡ ፈድፋደ፤

ነገሥታቱ፡ ፈጽመው፡ ከፉ፡

፫፤ ወሐነፀት፡ ጢሮስ፡ ወሲዶና፡ አፅዋኒሃ፤

ጢሮስ፡ ሲዶና፡ አምባዋን፡ ቆረቈረች፤

ወዘገበት፡ ብሩረ፡ ከመ፡ መሬት፤

ብሩን፡ እንደመሬት፡ አብዝታ፡ ሰበሰበች፤

ወአስተጋብአት፡ ወርቀ፡ ከመ፡ ፅንጕነ፡ ፍኖት፤

በጐዳና፡ እንዳለ፡ ትቢያ፡ ወር ቁን፡ አብዝታ፡ ሰበሰበች፤

፬፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ይወርስ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤ ዘሩባቤል፡ የኪ ራምን፡ ከብት፡ ይወርሳል፤

ወይኤዝዝ፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ኃይላ፤

ገንዘቧን፡ ወደባሕር፡ ይጥል፡ ዘንድ፡ ያዝዛል፤ ናቡከደነፆር፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ ኪራም፡ ገንዘቡን፡ እያነሣ፡ ከባሕር፡ ጥሎታል፤

ወይእቲኒ፡ በእሳት፡ ትጠፍዕ፤

ይህቺም፡ በጦር፡ ትጠፋለች፤

፭፤ ወትሬኢ፡ አስቀሎና፡ ወትፈርህ፤

አስቀሎና፡ የዚያችን፡ ጥፋት፡ ዓይታ፡ ትፈራለች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወጋዛሂ፡ ትደነግፅ፡ ፈድፋደ፤

ጋዛም፡ ፈጽማ፡ ትደነግጣለች፤

ወአቃሮንሂ፡ እስመ፡ ተኃፍረት፡ በጌጋያ፤

አቃሮንም፡ ትደነግጣለች፤ በኃጢአቷ፡ መከራ፡ መጥቶባት፡ አፍራለችና፤

ወይትኃጐል፡ ንጉሥ፡ እምጋዛ፤

ከጋዛ፡ ንጉሥ፡ ይጠፋል፤

ወአስቀሎናሂ፡ ኢትኄሉ፡ እንከ፤

አስቀሎናም፡ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ በተድላ፡ በደስታ፡ አትኖርም፤

፮፤ ወይነብሩ፡ እንከ፡ ካልዓን፡ አሕዛብ፡ ውስተ፡ አዛጦን፤

በአዛጦን፡ ሌሎች፡ አሕዛብ፡ ይኖሩባታል፤

ወእሥዕር፡ ፅዕለተ፡ ኢሎፍሊ፤

የኢሎፍላውያንን፡ ስድብ፡ አጠፋለሁ፤

፯፤ ወአአትት፡ ደሞሙ፡ እምአፉሆሙ፤

ስድባቸውን፤ አንድም፡ አጽንተው፡ የያዙትን፡ የእስራኤልን፡ ገንዘብ፡ ከነሱ፡ አርቃለሁ፤

ወርኵሶሙ፡ እማዕከለ፡ ስነኒሆሙ፤

አጽንተው፡ የያዙትን፡ ጣዖቱን፡ ከልቡናቸው፡ አጠፋዋለሁ፤

ወይትርፍ፡ ውእቱ፡ ለአምላክነ፤

ይህ፡ ጥፋቱ፡ ለፈጣሪያችን፡ ምልክት፡ ሆኖ፡ ይቀራል፤

ወይከውኑ፡ ከመ፡ መሳፍንተ፡ ይሁዳ፤

በይሁዳ፡ ተሹመው፡ እንደ፡ ነበሩ፡ እንደነ፡ ኢኮንያን፡ እንደነ፡ ሴዴቅያስ፡ ይሆናሉ፤

ወአቃሮንሂ፡ ከመ፡ ኢያውሴዎን፤

አቃሮንም፡ በኢያሱ፡ ጊዜ፡ እንደጠፋች፡ እንደ፡ ኢያውሴዎን፡ ትሆናለች፤

፰፤ ወአኀሥእ፡ ቤትየ፡ ወአቀውም፤

ወገኔን፡ በረድኤት፡ አጸናዋለሁ፤

ከመ፡ ኢትሑሩ፡ ወኢትግብኡ፤

በኢኮንያን፡ ተማርካችሁ፡ በዘሩባቤል፡ እንደተመለሳችሁ፡ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ አትመለሱም፤

ወኢየኃልፍ፡ እንከ፡ ዘያደነግፆሙ፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ የሚያስደነግጣችሁ፡ አሕዛብ፡ አይመጣም፤

እስመ፡ ይእዜ፡ ርኢኩ፡ በአዕይንትየ፤

በአሕዛብ፡ የሚመጣውን፡ መቅሠፍት፡ በዓይኔ፡ ዓይቻለሁና፤

፱፤ ተፈሥሒ፡ ፈድፋደ፡ ወለተ፡ ጽዮን፤

የጽዮን፡ ልጅ፡ ፈጽሞ፡ ደስ፡ ይበልሽ፤



ወሰብኪ፡ ወለተ፡ ኢየሩሳሌም፤

የኢየሩሳሌም፡ ልጅ፡ የሚጠትን፡ ነገር፡ ተጨዋወች፤ አንድም፡ የኦሪት፡ የወንጌል፡ ልጅ፡ ደስ፡ ይበልሽ፤

እስመ፡ ናሁ፡ ይመጽእ፡ ንጉሥኪ፡ ጻድቅ፤

ጻድቅ፡ ንጉሥ፡ ዘሩባቤል፡ ይነግሣልና፤

ወመድኀን፡ ወየዋህ፡ ውእቱ፤

የሚያድን፡ ዘሩባቤል፡ ይመጣልና፤ አንድም፡ የባሕርይ፡ አምላክ፡ ክርስቶስ፡ ይመጣልና፤ ዓለሙን፡ የሚያድን፡ ኃዳጌ፡ በቀል፡ ክርስቶስ፡ ይመጣልና፤

ወይጼዐን፡ ዲበ፡ አድግ፡ ወዲበ፡ ዕዋል፤

በናቲቷም፡ በልጇም፡ አህያ፡ ተቀምጦ፡ ይመጣል፤ አንድም፡ አሕዛብን፡ ልጆቻቸውን፡ ሊያሳምን፡ ይመጣል፤

፲፤ ወያጠፍዕ፡ ሠረገላ፡ እምኤፍሬም፡ ወአፍራሰ፡ እምኢየሩሳሌም፤

ከኤፍሬም፡ ሠረገላውን፡ ከኢየሩሳሌም፡ ፈረሶችን፡ ያጠፋል፤ ዘመኑ፡ ዘመነ፡ ሰላም፡ ሆኖ፤ አንድም፡ አጋንንትን፡ ከምእመናን፡ ያርቃል፤

ወየሐልቅ፡ እንከ፡ ቀስት፡ ወቀትል፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ሰልፍ፡ ይቀራል፤

ወይከውን፡ እንከ፡ ብዙኀ፡ ሰላም፡ እምአሕዛብ፤

ከአሕዛብ፡ ጥፋት፡ የተነሣ፡ በዘሩባቤል፡ ዘመን፡ ብዙ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይሆናል፤ አንድም፡ በጌታ፡ ዘመን፡ ብዙ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይደረጋል፤

ወይወርድ፡ ማይ፡ እስከ፡ ባሕር፤

ውሃው፡ እስከ፡ ውቅያኖስ፡ ድረስ፡ ይሄዳል፤ ትምህርት፡ በሀገሩ፡ ሁሉ፡ ይነገራል፤ አንድ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ይሰጣል፤

ወአፍላግ፡ ወሄላ፡ ምድር፤

ውሀው፡ ይወርዳል፤ ነገሥታቱ፡ ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ ይገዛሉ፤ ምንጭ፡ ይመነጫል፤ አንድም፡ ትምህርቱ፡ በሀገሩ፡ ሁሉ፡ ይነገራል፤

፲፩፤ ወአንተ፡ በደመ፡ ሥርዓት፡ ፈነውኩ፡ ሙቁሐኒኪ፡ እምአዘቅት፡ ዘአልቦ፡ ማይ፤

ሕግ፡ ኦሪት፡ በጸናበት፡ በደመ፡ በግዕ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ከሌለበት፡ ከግብጽ፡ አወጣኋችሁ፤ አንድም፡ ሕግ፡ ወንጌል፡ በጸናበት፡ በሥጋዬ፤ በደሜ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ከሌለበት፡ ከገሃነም፡ አወጣኋችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወይነብሩ፡ ውስተ፡ አጽዋን፡ ሙቁሐን፡ ተዓይን፤

በግብፅ፡ ተግዘው፡ ይኖሩ፡ የነ በሩ፡ እስራኤል፡ በኢየሩሳሌም፡ ይኖራሉ፤ አንድም፡ በሲኦል፡ ተግዘው፡ የነበሩ፡ ነፍሳት፡ በገ ነት፡ ይኖራሉ፤

ወህየንተ፡ አሐቲ፡ ዕለት፡ ካዕበተ፡ እፈድየኪ፤

ስለ፡ አንዲት፡ ቀን፡ እጽፍ፡ አድ ርጌ፡ እከፍልሻለሁ፡ አለ፣ በኋላ፡ የተደረገላቸው፡ ተድላ፡ ደስታ፡ በዝቶላቸዋልና፤

፲፫፤ እስመ፡ መሰጥኩከ፡ መንገ ሌየ፡ ይሁዳ፤

ሰሐብኩከ፡ አቅረብኩከ፡ ሲል፡ ነው፤ ይሁዳ፡ ወደኔ፡ አቅርቤ ሻለሁና፤

ወከመ፡ ቀስት፡ መላዕክም፡ ለኤፍሬም፣

አኃዝክም፡ ሲል፡ ነው፣ አሥ ሩን፡ ነገድ፡ በረድኤት፡ ያዝሁት፤

ወአነሥኦሙ፡ ለደቂቅኪ፡ ጽዮን፡ ላዕለ፡ ደቂቀ፡ ዮናናውያን፤

የመቃብያንን፡ ነገር፡ ይናገራል፣ ጽዮን፡ ልጆችሽን፡ በፅርዓውያን፡ ላይ፡ አስለጥናቸዋለሁ፤ አን ድም፡ ሐዋርያትን፡ በአሕዛብ፡ በአጋንንት፡ ላይ፡ አሠለጥና ቸዋለሁ፤

ወእሬስየኪ፡ ከመ፡ ኲናተ፡ መስተቃትል፣

በአርበኛ፡ እጅ፡ እንዳለ፡ ጦር፡ አደርግሻለሁ፡ ማለት፡ የዘሩባ ቤልን፡ ሥልጣን፡ እንደ፡ ዳዊት፡ አደርገዋለሁ፤

፲፬፤ ወትወፅእ፡ ማዕበል፡ ከመ፡ መብረቅ፣

መብረቅ፡ ፈጥኖ፡ እንዲሰማ፡ ረድኤት፡ ፈጥና፡ ትሰጣለች፤ አንድም የወልድ፡ ሥልጣን፡ በዕለተ፡ ምጽአት፡ አይሁድን፡ ያስደነግጣል፤

ወእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ይነፍሕ፡ በቀርን፣

ቀርነ፡ ሲል፡ ነው፤ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ነጋሪ ቱን፡ ይመታል፣ ነጋሪቱን፡ እየ መቱ፡ ከባቢሎን፡ ሲወጡ፡ አይ ለያቸውምና፤ አንድም፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ እለ፡ ውስተ፡ ሲኦል፡ ባዑ፡ ይላል፤

ወየሐውር፡ መዓቱ፡ ከመ፡ ዓውሎ፡ ቴማን፣

መዓቱ፡ እንደ፡ ሰማይ፡ አውሎ፡ ፈጥኖ፡ ይመጣል፤ አንድም፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ አጋንንትን፡ ያጠፋል፤

፲፭፤ ወእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመ ልክ፡ ይሠውቆሙ፡ ለሕዝቡ፣

ወገኖቹ፡ እስራኤልን፡ በረድኤት፡ ይደግፋቸዋል፤ አንድም፡ ምእመ ናንን፡ በረድኤት፡ ይጋርዳቸዋል፤



ወየሐልቅዎሙ፡ ወይነድፍዎሙ፡ በዕብነ፡ ሞጸፍ፣

በምድር፡ ነጉድ፡ ደንጊያ፡ ያጠ ፋቸዋል፤ አንድም፡ በነፍጥ፡ ያጠፋቸዋል፤ አንድም፡ በሥ ልጣን፡ ያጠፋቸዋል፤ አንድም፡ አጋንንትን፡ በመስቀል፡ ድል፡ ይነሷቸዋል፤

ወይሰትይዎሙ፡ ከመ፡ ወይን፣

እንደ፡ ወይን፡ ይጠጧቸዋል፡ ማለት፡ ገንዘባቸውን፡ አብዝተው፡ ይሰበስባሉ፤ አንድም፡ አሕዛብን፡ እንደ፡ እስራኤል፡ ያሳምኗቸዋል፤

ወይመልዑ፡ ምሥዋዓ፡ ከመ፡ ዘይት፣

መሥዋዕቱን፡ እንደ፡ ወይን፡ አብዝተው፡ ይሠዋሉ፤ አንድም፡ እስራኤል፡ የአሕዛብን፡ ደም፡ ያፈስሳሉ፤

፲፮፤ ወያድኅኖሙ፡ እግዚአብሔር፡ ይእተ፡ አሚረ፡ ከመ፡ አባግዕ፡ ለሕዝቡ፣

ያን፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ በሚ ጠት፡ ወገኖቹን፡ እንደ፡ በግ፡ ይጠብቃቸዋል፤

እስመ፡ አዕናቍ፡ ቅዱሳት፡ ያንኰረ ኵራ፡ ውስተ፡ ምድር፣

ስምንቱ፡ ደቂቀ፡ ክስሙናይን፡ በተባርዮ፡ ይገዟችዋልና፡ እነ ዚህም፡ ስምዖን፣ ይሁዳ፣ ናታን፣ እስራኤል፣ ማታትዩ፣ እስክን ድር፣ አርትቦሎስ፡ አትሮብሎስ፡ ናቸው፤ አንድም፡ ሐዋርያት፡ በመምህርነት፡ በኢየሩሳሌም፡ ይኖራሉ፤

፲፯፤ እስመ፡ ሠናይኒ፡ ሎቱ፡ ወበረ ከትኒ፡ ኀቤሁ፣

ያሥሩ፡ ነገድ፣ የሁለቱ፡ ነገድ፡ ሚጠት፡ ከሱ፡ ዘንድ፡ ነው፤

እክለ፡ ለወራዙት፣

ለሕፃናት፡ እህል፡ ይሰጣል፤

ወይነ፡ ወዕፍረተ፡ መዓዛ፡ ሰአሉ፡ እም ኀበ፡ እግዚአብሔር፣

ወይኑን፡ መዓዛ፡ ያለውን፡ ሽቱ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ለምኑ፣ ይሰጣችኋል።

## ምዕራፍ ፲

፩፤ ዝናመ፡ ፀደይ፣

የበልጉን፡ ዝናም፣

ወመፀው፣

የገፋን፡ ዝናም፤

እግዚአብሔር፡ ገብረ፡ ለምትሐተ፡ ዓይን፣

እግዚአብሔር፡ ያይን፡ ምሳ፡ አደረገው፡ ማለት፡ ለጊዜው፡ ደስ፡ ያሰኛል፤ አንድም፡ የነቢያትን፣ የሐዋርያትን፡ ትምህርት፡ ይሰጣል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይሁቦሙ፡ እግዚአብሔር፡ ዝናመ፡ ተወን።

የበልጉን፡ ዝናም፡ ይሰጣል።

ወያበቍል፡ ሣዕረ፡ ውስተ፡ ገዳም።

በምድረ፡ በዳ፡ ሣሩን፡ ያበቅላል።
ዘሩን፡ ተክሉን፡ ያበቅላል።

፪፤ እስመ፡ እለ፡ ይትዋሥኡ፡ ነበቡ፡ ዓመፃ።

የሚከራከሩ፡ ነቢያት፡ ሐሰት፡ ነገር፡ ተናገሩ።

ወእለ፡ ያስግሉ፡ ርእዩ፡ ሐሰተ።

የሚጠነቍሉ፡ ሰዎች፡ ሐሰት፡ ነገር፡ ተናገሩ።

ወሐለሙ፡ ሕልመ፡ ሐሰት።

ሐሰተኛ፡ ሕልም፡ አለሙ።

ወነገሩ፡ ከንቶ፡ ወመሀሩ።

ከንቱ፡ ነገርን፡ አስተማሩ።
ከንቱ፡ ነገርን፡ ተናገሩ።

ወበእንተ፡ ዝንቱ፡ ደወዩ፡ ከመ፡ አባግዕ፡ ወየብሱ።

ስለዚህ፡ ነገር፡ ቃባ፡ እንደያዘው፡ በግ፡ መከራ፡ ተቀበሉ።

እስመ፡ አልቦሙ፡ ሣህል፡ ለኖሎት።

ለነገሥታቱ፡ ይቅርታ፡ የላቸ ውምና።

፫፤ እስመ፡ ነደት፡ መዓትየ።

ቁጣዬ፡ በአሕዛብ፡ ላይ ስለሆነች።

ወእዋህዮሙ፡ ለአባግዕየ።

ወገኖቼ፡ እስራኤልን፡ በረድ ኤት፡ እጐበኛቸዋለሁ።

ወይሔውፆሙ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፡ ለመርዔቱ፡ ወለቤተ፡ ይሁዳ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ አሥሩን፡ ነገድ። ሁለቱን፡ ነገድ፡ በረድኤት፡ ይጐበኛቸዋል።

ወይሬስዮሙ፡ ከመ፡ ፈረስ፡ ሥሙር፡ ለፀር።

ድልው፡ ሲል፡ ነው። ለሰልፍ፡ እንደተዘጋጀ፡ ፈረስ፡ ያደርጋ ቸዋል።

፬፤ ወእምኔሁ፡ ርእየ።

ከደቂቀ፡ ክስሙናይን፡ አንዱንም፡ አንዱን፡ በዓይነ፡ መዓት፡ አየ።

ወእምኔሁ፡ ይወጽእ፡ ኵሉ፡ ዘይነድዕ፡ ቦቱ።

ከይሁዳ፡ መቅብያዊ፡ እስራኤ ልን፡ የሚጠብቅበት፡ ሥልጣን፡ ኃይል፡ ከእሱ፡ ይገኛል።

፭፤ ወይከውኑ፡ ከመ፡ ዘይከይዱ፡ ፅንጉነ፡ መርህብ።

በአደባባይ፡ እንደሚረገጥ፡ ጭቃ፡ ይሆናሉ።

እንዘ፡ ይትበዓሱ፡ በፍኖተ፡ ቀትል።

በአደባባይ፡ እ



ወይረውድዎሙ።

አሕዛብ፡ እስራኤልን፡ ይከቧ ቸዋል።

ወኢይክልዎሙ።

እስራኤልን፡ አይችሏቸውም።

እስመ፡ እግዚአብሔር፡ ምስሌሆሙ።

እግዚአብሔር፡ በረድኤት፡ ከነሱ፡ ጋራ፡ አለና።

ወይትሀፈሩ፡ መስተፅዕናነ፡ አፍራስ።

በፈረስ፡ የተቀመጡ፡ ሰዎች፡ መከራ፡ መጥቶባቸው፡ ያፍራሉ።

፮፤ ወአጸንዖ፡ ለቤተ፡ ይሁዳ።

የይሁዳን፡ ወገን፡ አጸናዋለሁ።

ወአድኅኖ፡ ለቤተ፡ ዮሴፍ።

የዮሴፍን፡ ወገን፡ አድነዋለሁ።

ወእመይጦሙ፡ እስመ፡ አፍቀርክዎሙ።

ወድጃቸዋለሁና፡ ከባቢሎን፡ ወደ ኢየሩሳሌም፡ እመልሳቸዋለሁ።

ወይከውኑ፡ ከመ፡ አመ፡ ሜጥክዎሙ።

ከግብፅ፡ እንደ፡ አወጣኋቸው፡ ጊዜ። መቃብያን፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከሦስት፡ ወር፡ በኋላ፡ ይመለሳሉ።

እስመ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፡ እሰጠዎሙ።

ፈጣሪያቸው፡ እኔ፡ ነኝና፡ በረ

፯፤ ወይከውኑ፡ ከመ፡ መስተቃ ትላነ፡ ኤፍሬም።

መቃብያን፡ ደቂቀ፡ ኤፍሬም፡ ይዌስቁ፡ ወይነድፉ፡ እንዳላቸው፡ ይሆናሉ። አንድም፡ ዕርዓው ያን፡ ወተገፍትዖ፡ አመ፡ ዕለተ፡ ቀትል፡ እንዳላቸው ይሆናሉ።

ወይትፌሣሕ፡ ልቦሙ፡ ከመ፡ ዘበወይን።

ወይን፡ የጠጣ፡ ሰው፡ ደስ፡ እንዲለው፡ ደስ፡ ይላቸዋል።

ወይሬእዩ፡ ውሉዶሙ፡ ወይትኃሠዩ።

ልጆቻቸውን፡ አይተው፡ ደስ፡ ይላቸዋል።

ወይትፌሣሕ፡ ልቦሙ፡ በእግዚአብሔር።

በእግዚአብሔር፡ አምነው፡ ደስ፡ ይላቸዋል።

፰፤ እትኤመሮሙ፡ ወእትዌከፎሙ።

ተገልጬ፡ በረድኤት፡ እቀበላ ቸዋለሁ።

እስመ፡ አነ፡ እባልሖሙ፡ በከመ፡ ብዝ ኆሙ፡ እምነበ፡ ዘረውክዎሙ፡ ውስተ፡ አሕዛብ።

እንደብዛታቸው፡ መጠን፡ ከበተ ንኋቸው፡ ከአሕዛብ፡ አገር፡ አወጣቸዋለሁ።

፱፤ ወእለሂ፡ ርኁቃን፡ ይዜክሩኒ።

በሩቅ፡ ያሉ፡ አሕዛብም፡ ያም ኑብኛል።

www.ethiopianorthodox.org

ወየሐፅኑ፡ ውሉደሙ፡ ወይትመየጡ፤

ልጆቻቸውን፡ እያሳደጉ፡ ይመ
ለሳሉ፤

፲፤ ወእመይጠሙ፡ እምድረ፡ ግብፅ፤

ከግብፅ፡ አወጣቸዋለሁ፤

ወእትሜጠዎሙ፡ እምፋርስ፡ ወእወስ
ዶሙ፡ ገለዓድ፤

ከፋርስ፡ አውጥቼ፡ ወደ፡ ገለ
ዓድ፡ እወስዳቸዋለሁ፤

ወውስተ፡ ሊባኖስ፤

ከዚያውም፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ደጋው፡
እወስዳቸዋለሁ፤

ወኢይተርፍ፡ አሐዱ፡ እምኔሆሙ፤

ከነዚያ፡ አንዱ፡ አይቀርም፤

፲፩፤ ወየኃልፉ፡እንተ፡ባሕር፡ጸባብ፤

በጠባቡ፡ ባሕር፡ መካከል፡
ይሄዳሉ፤

ወይከይዱ፡ ዲበ፡ ማዕበለ፡ ባሕር፤

እየተዋጉ፡ ከከተማው፡ ይወጣሉ፤

ወይየብሱ፡ ኵሉ፡ ቀላያተ፡ አፍላግ፤

ፈሳሽ፡ ውኆች፡ የሚሔዱበት፡
ወንዞች፡ ሁሉ፡ ደረቁ፤ አንድም፡
የነገሥታቱ፡ ሠራዊት፡ ጠፉ፤

ወይሠዐር፡ ኵሉ፡ ዕበለተ፡ ፋርስ፤

በፋርስ፡ ስድብ፡ ሁሉ፡ ይጠፋል፤

ወይትአተት፡ ኵሉ፡ በትረ፡ ትዕይርተ፡
ግብፅ፤

የግብፅ፡ ንጉሥ፡ ይጠፋል፤ አን
ድም፤ ትዕይርተ፡ በትረ፡ ግብፅ፡
ይላል፤ የንጉሡ፡ ተግዳሮት፡
ይጠፋል፤

፲፪፤ ወአጸንዖሙ፡ አነ፡ እግዚአብ
ሔር፡ አምላኮሙ፤

ፈጣሪያቸው፡ እኔ፡ አጸናቸዋለሁ፤

ወይትሜክሑ፡ በስምየ፤

በስሜ፡ አምነው፡ ይመካሉ።

## ምዕራፍ ፲፩

፩፤ አርኁ፡ አናቅጺከ፡ ሊባኖስ፤

ብልጣሶር፡ አንጥያኩስ፡ ደጅህን፡
ክፈት፤

ወትብላዕ፡ እሳት፡ አርዘከ፤

እሳት፡ ዛፍህን፡ ትብላው፡ ማለት፡
ጦር፡ ሠራዊትህን፡ ታጥፋው፤

፪፤ ለየዐይ፡ ቢሩሽ፤

ቢሩስ፡ ጽኑ፡ እንጨት፡ ነው፤
እንጨቱ፡ ይቃጠል፡ ማለት፡
አርበኛው፡ ይጥፋ፤

እስመ፡ ወድቀ፡ ዘግባ፤

ዘግባው፡ ወድቋል፡ ማለት፡
ንጉሡ፡ ጠፍቷልና፤



እስመ፡ ፈድፋደ፡ ሐስሩ፡ መኳንንት፤

መኳንንቱ፡ ፈጽመው፡ ተዋረዱ፡
እኮን፤

ለየዐይ፡ ዖመ፡ ባሳን፤

የባሳን፡ ዛፍ፡ ይቃጠል፡ ማለት፡
አርበኛው፡ ይጠፋል፤

እስመ፡ ተገዝመ፡ ዖም፡ ሐዲስ፡ ተክል፤

አዲሱ፡ ተክል፡ ዛፍ፡ ተቆርጧ
ልና፤ አንድም፡ ንጉሡ፡ ብልጣ
ሶር፡ ጠፍቷልና፤

፫፤ ቃለ፡ ኖሎት፡ እለ፡ ያስቈቅዉ፤

ይሰማዕ፡ ያለበት፡ ነው፤

በዌዋዌ፡ የሚያዝኑ፡ የሚያለ
ቅሱ፡ የነገሥታቱ፡ ድምፅ፡ ይሰ
ማል፤ አንድም፡ የነቢያት፡ የካ
ህናት፡ ልቅሶ፡ ይሰማል፤

እስመ፡ ሐስረ፡ ቃለ፡ አናብስት፡ እለ፡
ይጥኅሩ፤

ሲናገሩ፡ ያስፈሩ፡ የነበሩ፡ የነገ
ሥታቱ፡ ድምፅ፡ ጠፍቷልና፤

እስመ፡ ሐስረ፡ አድያመ፡ ዮርዳኖስ፤

ዘይኄንን፡ ያለበት፡ ነው፤ የዮር
ዳኖስን፡ አውራጃ፡ የሚገዛ፡
ንጉሡ፡ ጠፍቷልና፤

፬፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡
ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡
እንደ ሀ፡ [illegible]፤

ረዓይዎን፡ ለአባግዓ፡ ቀትል፤

ነቢያት፡ ካህናት፡ ሰልፍ፡ የሚ
ወዱ፡ እስራኤልን፡ ጠብቋቸው፤

፭፤ ወእለሂ፡ አድምዑ፡ ረገዙ፡
ወኢነስሑ፤

ባለሟልነትን፡ ያገኙ፡ ሦስቱ፡
ካህናት፡ እየወጉ፡ ጣሏቸው፡
አላዘኑም፤

ወእለሂ፡ ይሠይጥዎን፡ ይቤሉ፡ ይትባ
ረክ፡ እግዚአብሔር፤

ለሴት፡ ለመሸታ፡ የሚሸጧቸው፡
ሰዎች፡ እግዚአብሔር፡ ይክበር፡
ይመስገን፡ አሉ፤

እስመ፡ ብዕልነ፤

እነዚያን፡ ሸጠን፡ ከብረናልና፤

ወእለሂ፡ ይርዕይዎን፡ ኢያጽዕቅዎሙ፡
ወኢምንትኒ፡ በእንቲአሁ፤

የሚጠብቋቸውንም፡ ሰዎች፡
ምንም፡ ምን፡ አላስጨነቋቸውም፤

፮፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ኢይምሕኮሙ፡
ለእለ፡ ይነብሩ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ይቤ፡
እግዚአብሔር፤

ስለዚህ፡ ነገር በዚህ፡ ዓለም፡ የሚ
ኖሩትን፡ ሰዎች፡ ይቅር፡ አልላቸ
ውም፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

ወናሁ፡ አነ፡ አገብዖ፡ ለሰብእ፡ ለለ፩፡ ፩ዱ፡
ውስተ፡ እደ፡ ካልዑ፤

እነሆ፡ አንዱንም፡ አንዱንም፡ ሰው፡
በአንዱ፡ እጅ፡ እጥለዋለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወውስተ፡ እደ፡ ንጉሥ፤
በንጉሡ፡ እጅ፡ እጥላቸዋለሁ፤
ወያኃልቅዋ፡ ለምድር፤
ምድርን፡ ያጠፏታል፤
ወኢያድኅኖሙ፡ እምእዴሆሙ፤
ሦስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ ከእ
ጃቸው፡ አላድናቸውም፤

፯፤ ወእርዕዮን፡ ለአባግዓ፡ ቀትል፡
ውስተ፡ እደ፡ ከነዓን፡ (ከናንዩ)፤
ሰልፍ፡ የሚወዱ፡ እስራኤልን፡
በንዑሳን፡ ካህናት፡ እጅ፡ እጠ
ብቃቸዋለሁ፤
ወአነሥእ፡ ሊተ፡ ፪ተ፡ አብትረ፤
ንጉሡን፡ ሊቀ፡ ካህናቱን፡ አስ
ነሣለሁ፤
ለአሐቲ፡ ሰመይክዋ፡ ስነ፤
አንዲቱን፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ አልኋት፤
ወለካልዕታ፡ ሐብለ፤
ሁለተኛይቱን፡ ንጉሥ፡ አልኋት፤
ወእርዕዮን፡ ለአባግዕየ፤
መቃብያንን፡ እጠብቃቸዋለሁ፤

፰፤ ወአጠፍእሙ፡ ለ፫ቱ፡ ኖሎት፡
በአሐዱ፡ ወርኅ፤
ስምዖንን፤ አልፍሞስን፤ መባ
ልስን፡ በአንድ፡ ወር፡ አጠፋቸ
ዋለሁ፤ አንዱን፡ በሰይፍ፡ አስ
መትቶ፡ አስቅሎታል፤ ሁለተኛ
ውን፡ በቁርበት፡ ጠቅሎ፡ ከባ
ሕር፡ አስጥሎታል፤ ሦስተኛው፡
የደረሰበት፡ ጠፍቷል፤
ወትከብድ፡ ነፍስየ፡ በላዕሌሆሙ፤
ልቡናዬ፡ በነዚያ፡ ላይ፡ ጸናች፤
እስመ፡ ነፍሶሙ፡ ግዕረት፡ ላዕሌየ፤
ሰውነታቸው፡ እኔ፡ ስለአመጣ
ሁባቸው፡ መከራ፡ አዝናለችና፤

፱፤ ወእቤሎሙ፡ ኢይርዒክሙ፡ እንዘ፡
ትብሉ፡ ዘሞተሂ፡ ለይሙት፡ ወዘደክ
መሂ፡ ለይድክም፤
የሞተው፡ ይሙት፡ የደከመው፡
ይድከም፡ እያላችሁ፡ አልጠበቃ
ችኋቸውም፡ አልኋቸው፤
ወዘሂ፡ ተርፈ፡ ለይብላዕ፡ ሥጋ፡ ቢጹ፤
ከሞት፡ የቀረው፡ የባልንጀራውን፡
ገንዘብ፡ ይብላ፡ እያላችሁ፡ አል
ጠበቃችኋቸውም፤

፲፤ ወእነሥእ፡ ለበትርየ፡ ለስን፡
ወእገድፋ፤
ስን፡ ያልኋት፡ ብትሬን፡ አን
ሥቼ፡ እጥላታለሁ፡ ማለት፡
ሊቀ፡ ካህናቱን፡ አጠፋዋለሁ፤
ከመ፡ እሚጥ፡ ኪዳንየ፡ ዘተካየድኩ፡
ምስለ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ፤
ከእለ፡ አብርሃም፡ ጋራ፡ የተ
ማማልኩትን፡ መሐላ፡ እለውጥ፡
ዘንድ፤



፲፩፤ ወእትመየጥ፡ ይእተ፡ አሚረ፤
ያን፡ ጊዜ፡ ከመዓት፡ ወደ፡ ምሕ
ረት፡ እመለሳለሁ፤
ወየአምርዎን፡ ከናንዩ፡ ለአባግዕየ፡ እለ፡
ተዓቅባ፤
ከሞት፡ የተጠበቁ፡ መቃብያንን፡
ንዑሳን፡ ካህናት፡ ይጠብቋ
ቸዋል፤
እስመ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ውእቱ፤
የእግዚአብሔር፡ ትእዛዝ፡ ነውና፤

፲፪፤ ወእቤሎሙ፡ እመ፡ አሥመ
ርክሙ፡ በቅድሜክሙ፡ ድልዉ፡ ሊተ፡
ወሀቡኒ፡ አስብየ፡ ሠላሳ፡ ብሩረ፤
በፊታችሁ፡ መክሬ፡ አስተምሬ፡
ያስ፡ አሰኘቻችሁ፡ እንደሆነ፡ ዋጋ
ዬን፡ ሠላሳ ብር፡ ስጡኝ፡ አል
ኋቸው፤

፲፫፤ ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔር፡ ደዮ፡
ውስተ፡ ሕንቅርት፡ ወፍትኖ፡ ለእመ፡
ጽሩይ፡ ውእቱ፤
ጽሩይነቱን፡ ሳታውቅ፡ እንዳት
ቀር፡ በከውር፡ አድርገህ፡ ፍተ
ነው፡ አለኝ፡ እግዚአብሔር፤
በከመ፡ አመከርዎ፡ እሙንቱ፤
እነዚያ፡ እንደፈተኑት፡ ማለት፡
ሕጉን፡ ሥርዓቱን፡ እንዳጠፉ፡
ሰውነታቸውን፡ እንዳሳደፉ፡
ነው፤
ወነሣእክዎ፡ ዘክሙ፡ ሠላሳ፡ ብሩረ፡ ወወ
ደይክዎ፡ ውስተ፡ ሕንቅርት፡ ዘቤተ፡
እግዚአብሔር፤
ሠላሳውን፡ ብር፡ ተቀብዬ፡ በቤተ፡
እግዚአብሔር፡ ከውር፡ አኖር
ሁት፡ ማለት፡ በባቢሎን፡ መከራ፡
ፈትኜ፡ በኢየሩሳሌም፡ አኖር
ኋቸው፤ ከዚህ፡ እንዲህ፡ አለ፤
ኢሳይያስ፡ ለምንት፡ ትሠይጡ፡
በወርቅ፡ አለ፤ አይጣላም፡ ቢሉ፡
አይጣላም፤ የዓመት፡ ልብስ፡
የዕለት፡ ጉርስ፡ ያለው፡ ገንዘብ፡
ሳይቀበል፡ ማስተማር፡ ይገባ
ልና፤ ኢሳይያስ፡ ለምንት፡ ትሠ
ይጡ፡ በወርቅ፡ አለ፤ የዕለት፡
ጉርስ፡ የዓመት፡ ልብስ፡ የሌ
ለው፡ ገንዘብ፡ ተቀብሎ፡ ማስ
ተማር፡ ይገባልና፡ ከዚህ፡
እንዲህ፡ አለ፤

፲፬፤ ወገደፍኩ፡ ካልዕተ፡ በትርየ፡
ሐብለ፤
ሐብል፡ ያልኋት፡ ሁለተኛይቱ፡
ብትሬን፡ ጣልኋት፡ ንጉሡን፡
አጠፋሁ፤
ከመ፡ እሚጥ፡ ምክናን፡ ዘማዕከለ፡
ይሁዳ፡ ወዘማዕከለ፡ እስራኤል፤
በዐሥሩ፡ ነገድና፡ በሁለቱ፡
ነገድ፡ ያለ፡ አገዛዝን፡ እመልስ፡
ዘንድ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፤ ወይቤለኒ: እግዚአብሔር: ዓዲ: ንሣእ: ለከ: ንዋየ: ኖሎት: ዘኖላዊ: አብድ፣

ዳግመኛ: የሰነፉን: ንጉሥ: ሹመት: እግዚአብሔር: ውሰድ: አለኝ፣

፲፮፤ እስመ: ናሁ: አነ: አነሥእ: ኖላዌ: ውስተ: ምድር፣

እኔ: በዚህ: ዓለም: እንዲህ: ያለ: ንጉሥ: አነግሣለሁና፤

ዘተገድፈሂ: ኢይረድዕ፣

የወደቀውን: የማያነሣ፤

ወዘተዘርወሂ: ኢያስተጋብዕ፣

የተበተነውን: መክሮ: አስተ ምሮ: የማይሰበስብ፤

ዘቈስለሂ: ኢይፌውስ፣

የቈሰለውን: የማያድን፣

ወዘሐይወሂ: ኢያረትዕ፣

ጥቂት: የተሻለውን: የማያቀና: ንጉሥ: አነግሣለሁና፤

ወይበልዕ: ሥጋ: ዘሰብሐ፣

የሰውን: ገንዘብ: ይበላል: እንጂ፤

ወያስተናግዕ: ዓገዳሆሙ፣

የድሆችን: ገንዘብ: ይበላል: እንጂ፤

፲፯፤ አሌሎሙ: ለእለ: ከንቶ: ይርዕዩ፣

ከንቱ: መጠበቅን: ለሚጠብቁ: ወዮላቸው፤

ወእለ: የኀድጉ: አባግዓ፣

መቃብያንን: የሚያጠፉ፤

መጥባሕት: ውስተ: መዝራዕተ: እዴሁ፣

በእጁ: ሾተል: አለ: ማለት: ሥልጣን: አለ፤

ወውስተ: ዓይኑ: ዘየማን፣

በቀኝ: ዓይኑም: ከፍና: ዝቅ: አድርጎ: ማየት: አለ፤

ወመዝራዕቱሂ: ዘየማን: የቢስ: ይየብስ፣

ቀኝ: ክንዱ: ይሰላል: ማለት: ሥልጣኑ: ይጠፋል፤

ወዓይኑሂ: ዘየማን: ነቋረ: ይነቍር፣

ቀኝ: ዓይኑ: ይጠፋል: ማለት: ከዓይነ: ልቡናው: እውቀት: ይጠፋል።

## ምዕራፍ ፲፪

፩፤ ተረፈ: ቃለ: እግዚአብሔር: ላዕለ: እስራኤል፣

እግዚአብሔር: በእስራኤል: ከማ ናገር: የቀረው: በአሕዛብ: ያና ገረው: ነገር: ይህ: ነው፤ አን ድም: በአሕዛብ: ያናገረው: ብዙ: ነገሩ: ይህ: ነው፣

ወይቤ: እግዚአብሔር: ዘሰፍሐ: ለሰማይ፣

ሰማይን: እንደ: ሙሴ: ድን ኳን: የዘረጋው: እሱ: ነው፤

ብሱን: ሲያ...



ወሣረረ: ለምድር፣

ምድርን: ያጸናት: እግዚአብ ሔር: እንዲህ: አለ፤

ወይፈጥር: ነፍሰ: ላዕለ: ሰብእ፣

አእምሮን: በሰው: የሚያሳድር: እሱ: ነው፤

፪፤ ናሁ: አነ: እሬስዮ: ለኢየሩሳሌም: ከመ: ድርኩኩተ: ማዕፆ: ዘኢይት ሀወክ፣

ኢየሩሳሌምን: እንደ: መዝጊያ: ወንዳወንዴ: አደርጋታለሁ: ያ: ወደውጭ: እንዳይወጣ: በሀ ገሯ: ጸንታ: ትኖራለች፤ አንድም: ዘይትሀወክ: ይላል፤ ያ: እን ዲታወክ: እንድትታወክ: አደ ርጋታለሁ፣

እምኵሉ: አሕዛብ: እለ: አድያም: ወእለ: ዓውዳ፣

በመወሳሰኛዋ: በዙሪያዋ: ካሉ: አሕዛብ: ተለይታ: ጸንታ: ትኖ ራለች፤

ወበይሁዳ: ይከውን: ጥቅመ: ኢየ ሩሳሌም፣

የኢየሩሳሌም: ቅጽር: በይሁዳ: ይሆናል: ማለት: ለምቶ: ቀንቶ: እስከ: ይሁዳ: ይደርሳል፤

፫፤ ይእተ: አሚረ: እሬስያ: ለኢየ ሩሳሌም: ከመ: ዕብን: እንተ: ይከይዱ: ኵሉ: አሕዛብ፣

ጊዜ: ኢየሩሳሌምን: ሰው: ... ያ:

አደርጋታለሁ፣ ያች: እንዳት ሰቀቅ: ኢየሩሳሌምም: መከራ ውን: እንዳትሰቀቅ: አደርጋ ታለሁ፤

ወኵሉ: ዘኬዳ: ይሣለቅ: ላዕሌሃ፣

በሷ: መከራ: የሚያመጣ: ሰው: ሁሉ: ይዘብትባታል፤ አንድም: በሷ: እዘብትባታለሁ: ማለት: ዘበት: ነው፤

ወይትጋብዑ: ኵሎሙ: ላዕሌሃ: አሕዛበ: ምድር፣

አሕዛብ: ሁሉ: በሷ: ላይ ይሰበሰባሉ፤

፬፤ ይእተ: አሚረ: ይቤ: እግዚአ ብሔር: ዘኵሎ: ይመልክ፣

ያንጊዜ: ሁሉን: የሚገዛ: እግ ዚአብሔር: እንዲህ: አለ፤

እቀሥፍ: ኵሎ: አፍራሰ: አሕዛብ: በድንጋጼ፣

የአሕዛብን: ፈረሶች: በቃታ: አጠፋለሁ፤

ወመስተፅዕናነ: በዝንጋጼ:

በፈረስ: የተቀመጡትንም: ሰዎች: አእምሯቸውን: አሳ ጥቼ: አጠፋቸዋለሁ፤

ወእከሥት: አዕይንትየ: ላዕለ: ቤተ: ይሁዳ:

ዓይነ: ምሕረቴን: በይሁዳ: ወገኖች: ላይ እገልጣለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእቀሥፍ፡ ኵሎ፡ አፍራሰ፡ አሕዛብ፡ በዐዊር፤

የአሕዛብን፡ ፈረሶች፡ በድንብር ብር፤ አንድም፡ በአንጋዳ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፭፤ ወይቤሉ፡ መሳፍንተ፡ ይሁዳ፡ ወእለ፡ ይነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፡ በልቦሙ፤ ረከብናሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ አምላክነ፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

የይሁዳ መሳፍንትና፡ በኢየሩሳሌም፡ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡ በልቡናቸው፤ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔርን፡ በረድኤት፡ አገኘነው፡ አሉ፤

፮፤ ይእተ፡ አሚረ፡ እሬስዮሙ፡ ለቤተ፡ ይሁዳ፡ ከመ፡ ትንታገ፡ እሳት፡ ማዕከለ፡ ዕፀው፤

በእንጨት፡ መካከል፡ እንዳለ፡ ትንታግ፡ እሳት፡ አደርጋቸዋለሁ፤ ያ፡ እንዲያጠፋ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወከመ፡ ነበልባለ፡ እሳት፡ ውስተ፡ ሣዕረ፡ ገዳም፤

በሳር፡ መካከል፡ እንዳለ፡ እሳት፡ አደርጋቸዋለሁ፤ ያ፡ እንዲያ ጠፋ፡ ያጠፋሉ፤

ወይበልዑ፡ ኵሎ፡ አሕዛብ፡ ዘዓውዶሙ፡ ዘየማኖሙ፡ ወዘጸጋሞሙ፤

በቀኝ፡ በግራ፡ በዙሪያቸው፡ ያሉ፡

ወትነብር፡ እንከ፡ ኢየሩሳሌም፡ ባሕቲታ፡

ኢየሩሳሌም፡ ጠላት፡ ጠፍቶ ላት፡ አርፋ፡ ትኖራለች፤

፯፤ ወያድኅን፡ እግዚአብሔር፡ አህጉረ፡ ይሁዳ፡ ከመ፡ ትካት፤

ከግብፅ፡ እንዳወጣቸው፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ የይሁዳን፡ አውራጃ፡ ይጠብቃል፤

ከመ፡ ኢያዕብዩ፡ ትዝኅርቶሙ፡ ላዕለ፡ ቤተ፡ ዳዊት፤

አሕዛብ፡ በዳዊት፡ ወገኖች፡ ላይ፡ ትዕቢታቸውን፡ እንዳያበዙ፤

ወትዝኅኤሆሙ፡ ለእለ፡ ይነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወላዕለ፡ ይሁዳ፤

በኢየሩሳሌምና፡ በይሁዳ፡ በሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ላይ በጠላትነት፡ መነሣታቸውን፡ እንዳያበዙ፤

፰፤ ወይእተ፡ አሚረ፡ ይቀውም፡ ሎሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለእለ፡ ይነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፤

ያንጊዜ፡ በኢየሩሳሌም፡ በሚኖሩ፡ ሰዎች፡ በረድኤት፡ ይቆምላቸዋል፤

ወውእተ፡ አሚረ፡ ዘድኩም፡ እምኔሆሙ፡ ይከውን፡ ከመ፡ ቤተ፡ ዳዊት፤

ያን፡ ጊዜ፡ ከሳቸው፡ ወገን፡ የሚሆን፡ ደካማው፡ [illegible]



ወቤተ፡ ዳዊት፡ ይከውን፡ ከመ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፤

የዳዊት፡ ወገን፡ እንደ፡ አብር ሃም፡ ይሆናል፤

ወከመ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ በቅድሜሁ፤

በፊቱ፡ እንደ፡ መልአክ፡ (ሰናክሬም) ይሆናል፤

፱፤ ወውእተ፡ አሚረ፡ እትኃሠሦሙ፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ ይመጽኡ፡ ኢየሩሳሌም፡ ከመ፡ አዕትቶሙ፤

ያንጊዜ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ የሚመጡ፡ አሕዛብን፡ በቂሮስ፡ በዳርዮስ፡ አድሬ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፲፤ ወእክዑ፡ ላዕለ፡ ቤተ፡ ዳዊት፡ ወላዕለ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፤

በዐሥሩ፡ ነገድ፤ በሁለቱ፡ ነገድ፤ ላይ፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ መንፈስ፡ ረድኤትን፡ አሣድራለሁ፤ አንድም፡ በሐዋርያት፡ በአርድዕት፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ አሳድራለሁ፤

ወውእተ፡ አሚረ፡ ሀለዎሙ፡ ይርአይዎ፡ ለዘወግዕዎ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ዕርአውያን፡ የወጉት፡ ይሁዳ፡ መቅብዩን፡ ያዩት፡ ዘንድ፡ አላቸው፤ አንድም፡ አይሁድ፡ የወጉት፡ ጌታን፡ ሐዋርያት፡ ያዩት፡ ዘንድ፡ አላቸው፤ የወጋው፡ አንድ፡ [illegible] እለምን፡

[illegible]

ቢሉ፡ መጽሐፍ፡ ምሥጢር፡ ይጠነቀቃል፡ እንጂ፡ አንድና፡ ብዙ፤ ሴትና ወንድ፤ ሩቅና፡ ቅርብ፡ አይጠነቀቅምና፤ አንድም፡ መውጋት፡ የሁሉ፡ ፈቃድ፡ ስለሆነ፡ ሺህ፡ ቢመክር፡ አንድ፡ ይወረውር፡ እንዲሉ፤ አንድም፡ መውጋት፡ ብቻ በጦር፡ ነው? በቀኖትም፡ ወግተውታልና፡ እንዲህ፡ አለ፤

ወይትመየጡ፡ ውስተ፡ ብካይ፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ወደለቅሶው፡ ይመለሳሉ፤

ይበክይዎ፡ ወይላሕውዎ፡ ከመ፡ ዘያፈቅርዎ፤

የሚወዱት፡ እንደመሆናቸው፤ እንደሚወዱት፡ ሰው፡ ያዝኑለታል፤ ያለቅሱለታል፤

ወየሐምሙ፡ ሕማመ፡ በኵር፤

እናት፡ ለበኵር፡ ልጇ እንድታዝን፡ ያዝኑለታል፤

፲፩፤ ውእተ፡ አሚረ፡ የዓቢ፡ ላሃ፡ ለኢየሩሳሌም፡ መጠነ፡ ውኂዝ፡ ዘይውኅዝ፡ በገዳም፤

ያንጊዜ፡ የኢየሩሳሌም፡ ልቅሶዋ፡ በምድረ፡ በዳ፡ እንደሚፈስ፡ ውሀ፡ ይበዛል፤

ወይላህዉ፡ ሕዝብ፡ ላሃ፡ በበሕዘቢሆሙ፤

በየወገናቸው፡ ልቅሶን፡ ያለቅሳሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወሕዝብኒ፡ በባሕቲቶሙ፤
ሕዝቡም፡ ብቻቸውን፡ ያለቅሳሉ፤
ወአንስትያሆሙኒ፡ ለባሕቲቶን፤
ሴቶችም፡ ብቻቸውን፡ ያለቅሳሉ፤
ሕዝበ፡ ቤተ፡ ዳዊት፡ በባሕቲቶሙ፤
የዳዊት፡ ወገኖች፡ ብቻቸውን፡ ያለቅሳሉ፡ አለ፤ ሌላ ዳዊት፡ ነው፤ አንድም፡ እሱ፡ ነው፤
ወአንስቲያሆሙኒ፡ ለባሕቲቶን፤
ሴቶቻቸውም፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ፤

፲፫፤ ሕዝበ፡ ቤተ፡ ናታን፡ ለባሕቲቶሙ፤
የናታን፡ ወገኖች፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ፡ አለ፤ ሌላ፡ ናታን፡ ነው፤ አንድም፡ እሱ፡ ነው፤
ወአንስቲያሆሙኒ፡ በባሕቲቶን፤
ሴቶቻቸውም፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ፤
ሕዝበ፡ ቤተ፡ ስምዖን፡ ለባሕቲቶሙ፤
የስምዖን፡ ወገኖች፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ፤ ሌላ፡ ስምዖን፡ ነው፤ አንድም፡ እሱ፡ ነው፤
ወአንስቲያሆሙኒ፡ ለባሕቲቶን፤
ሴቶቻቸውም፡ ለብቻቸው፡ ያለ
ሕዝበ ቤተ፡ ሌዊ፡ በባሕቲቶሙ፤
የሌዊ፡ ወገኖች፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ፤
ወአንስቲያሆሙኒ፡ በባሕቲቶን፤
ሚስቶቻቸውም፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ፤

፲፬፤ ወኵሉ፡ ሕዝብ፡ ዘተርፉ፡ ለባሕቲቶሙ፤
ከሞት፡ የቀሩት፡ ሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ፤
ወአንስቲያሆሙ፡ በባሕቲቶን፤
ሚስቶቻቸውም፡ ለብቻቸው፡ ያለቅሳሉ።

## ምዕራፍ ፲፫

### ጉባዔ

፩፤ ወውእቱ፡ አሚረ፡ ይትረኃዉ፡ ኵሉ፡ በሐውርተ፡ ቤተ፡ ዳዊት፤
ያን፡ ጊዜ፡ በሚጠት፡ የዳዊት፡ ወገኖች፡ ቤቶች፡ ይከፈታሉ፤ አንድም፡ ዕዝነ፡ ሰማዕያን፡ ይከፈታል፤

፪፤ ወከመዝ፡ ይከውን፡ ይእተ፡ አሚረ፤
ያንጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤
ወይጠፍዕ፡ አስማቲሆሙ፡ ለጣዖታት፡ እምኵሉ፡ ምድር፤
የጣዖታቱ፡ [illegible]



ወአልቦ፡ ዘይዜከሮሙ፡ እንከ፤
እንግዲህ፡ ወዲህ፡ የሚያስባቸው፡ የለም፤
ወያውዕይዎሙ፡ እምድር፡ ለሐሳውያነ፡ ነቢያት፤
ሐሳውያን፡ ነቢያትን፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ያጠፏቸዋል፤
ወለመንፈሰ፡ ሐሰት፤
ሐሰተኛ፡ ትንቢት፡ የሚናገሩትንም፡ ያጠፋቸዋል፤

፫፤ ወለእመኒ፡ ቦ፡ ዘተነበየ፡ ብእሲ፡ ይብልዎ፡ አቡሁ፡ ወእሙ፡ እለ፡ ወለድዎ፡ ሶበ፡ ተነበየ፡ ኢወለድናከ፤
ትንቢት፡ የተናገረ፡ ሰው፡ ቢኖር፤ ትንቢት፡ በተናገረ፡ ጊዜ፡ የወለዱት፡ አባቱና፡ እናቱ፡ አልወለድንህም፡ ይሉታል፤ አንድም፡ ጌታ፡ ትንቢት፡ ቢያናግር፡ የናቱ፡ የሐና፡ ያባቱ፡ የኢያቄም፡ ወገኖች፡ አይሁድ፡ የኛ፡ ወገን፡ አይደለህም፡ ይሉታል፤

፬፤ ይእተ፡ አሚረ፡ ይትኃፈሩ፡ ኵሎሙ፡ ነቢያት፡ በዘርእዩ፡ ወበዘተነበዩ፤
ያንጊዜ፡ ነቢያተ፡ ሐሰት፡ ባዩት፡ በተናገሩት፡ ነገር፡ ያፍራሉ፤ አንድም፡ ነቢያት፡ ትንቢት፡ በተ[illegible] ባዩት፡ ባሰሙት፡
[illegible]
ወይለብሱ፡ ሠቀ፡ ፀጉር፤
ምንጣፍ፡ ይለብሳሉ፤
እስመ፡ ሐሰዉ፤
ሀሰት፡ ትንቢት፡ ተናግረዋልና፤

፭፤ ወያርኢ፡ እዴሁ፡ ዘቈስለ፤
የቆሰለውን፡ እጁን፡ ያሳያል፤ አንድም፡ ጌታ፡ የተቸነከረውን፡ እጁን፡ ያሳያል፤
ወይብል፡ አንሰ፡ ኢኮንኩ፡ ነቢየ፡ አላ፡ መስተገብረ፡ ምድር፡ አነ፤
እኔ፡ የአሕዛብ፡ ወገን፡ አይደለሁም፤ አራሽ፡ ነኝ፡ እንጂ፡ ይላል፤ አንድም ጌታ፡ እኔ፡ ሩቅ፡ ብእሲ፡ አይደለሁም፤ ምድርን፡ የፈጠርሁ፡ የባሕርይ፡ አምላክ፡ ነኝ፡ እንጂ፤
ወለሰብእ፡ ተቀነይኩ፡ እምንዕስየ፤
ከሕፃንነቴ፡ ጀምሮ፡ ለሰው፡ ስገዛ፡ ኖርሁ፤ አንድም፡ ጌታ፡ ሰውን፡ የፈጠርሁ፡ እኔ፡ ነኝ፡ ይላል፤

፮፤ ወይብሎ፡ ምንትኑ፡ ዝንቱ፡ መቅሠፍት፡ ዘማዕከለ፡ እደዊከ፤
ይህ፡ በጅህ፡ መካከል፡ ያለው፡ ቁስል፡ ምንድነው፡ አለው፤
ወይብል፡ ቈሰልኩ፡ በቤተ፡ አርክየ፤
በወዳጄ፡ ቤት፡ ሞፈር፡ ቀምበር፡ ስጠርብ፡ ቆሰልሁ፡ አለ፤
[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ሲጠርብ፡ የቆሰለው፡ ነው፤ አን
ድም፡ በእጅህ፡ መካከል፡ ያለው፡
ይኽ፡ ቍኖት፡ ምንድነው፡ አለው፣
ይኽስ፡ ከአብርሃም፡ በነሣሁት፡
ሥጋ፡ ተቸነከርሁ፡ ይላል፤

፯፤ ተንሥኢ፡ ኵናት፡ ላዕለ፡ ኖሎት፣
ጦር፡ በነገሥታቱ፣ በካህናቱ፡
ላይ፡ ተነሽ፤
ወላዕለ፡ ብእሲ፡ ምስለ፡ ሀገሩ፣
ከሀገሩ፡ ጋራ፡ ለማጥፋት፡ በሰው፡
ላይ ተነሽ፤
ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣
ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡ አለ፤
እቀትሎ፡ ለኖላዊ፡ ወይዘረዉ፡ አባግዓ፡
መርዔቱ፣
ይሁዳ፡ መቅብያዊን፡ እገድለዋ
ለሁ፣ መቃብያን፡ ይበተናሉ፣
ለጌታ፡ የመቃብያን፡ ሞት፡ ፈቃዱ፡
ነው፤ እነዚያ፡ ግን፡ አትርፈው፡
ለሴት፣ ለመሸታ፡ ሸጠዋቸዋ
ልና፤ አንድም፡ ክርስቶስን፡ እገ
ድለዋለሁ፣ ሐዋርያቱ፡ ይበተ
ናሉ፣ ለአብ፡ የወልድ፡ ሞት፡
ፈቃዱ፡ ነው፤ እነዚያ፡ ግን፡
አትርፈው፡ ገርፈው፡ ሰቅለ
ውታልና፤

ወአመጽእ፡ እዴየ፡ ላዕለ፡ ኖሎት፣
በነገሥታቱ፣ በካህናቱ፡ እደ፡
መዓቴን፡ አመጣለሁ፤ አንድም፡
እደ፡ ምሕረቴን፡ አመጣለሁ፤

፰፤ ወአስተጋብዖሙ፡ እምኵሉ፡
ምድር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፣
ከሦስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡
በኋላ፡ ካራቱ፡ መዓዝን፡ እሰበ
ስባቸዋለሁ፡አለ፡ እግዚአብሔር፤
የኃልቅ፡ ፪ቱ፡ እድ፣
ሁለቱ፡ እጅ፡ ይጠፋል፤
ወይተርፍ፡ ሣልስተ፡ እዴሃ፡ ውስቴታ፣
ሢሶው፡ ይቀራል፣

፱፤ ወአወስዶሙ፡ ውስተ፡ እሳት፡
ለእልክቱ፡ ሣልስተ፡ እዴሆሙ፣
ሢሶውን፡ ወደመከራ፡ እወስ
ዳቸዋለሁ፤
ወአረስኖሙ፡ ከመ፡ ያረስንዎ፡ ለብሩር፣
ብርን፡ በእሳት፡ እንዲፈትኑት፡
በመከራ፡ እፈትናቸዋለሁ፤
ወእፈትኖሙ፡ ከመ፡ ይፈትንዎ፡
ለወርቅ፣
ወርቅን፡ በእሳት፡ እንዲፈትኑት፡
በመከራ፡ እፈትናቸዋለሁ፤
ወውእቱሰ፡ ይጼውእ፡ ስምየ፡ ይቤ፡
እግዚአብሔር፣
ይሁዳ፡ መቅብያዊ፡ ስሜን፡
ይጠራል፡ እ



ወአነሂ፡ እሰጠዎ፣
እኔ፡ እመልስለታለሁ፤
ወእብል፡ ሕዝብየ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፣
ይህ፡ ወገኔ፡ ነው፡ እለዋለሁ፣
ወውእቱ፡ ይብለኒ፡ እግዚአብሔር፡
አምላኪየ፡ አንተ፣
እሱም፡ ፈጣሪዬ፡ አንተ፡ ነህ፡
ይለኛል።

## ምዕራፍ ፲፬

፩፤ ናሁ፡ ይመጽእ፡ መዋዕል፡ ይቤ፡
እግዚአብሔር፣
እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡
ያለ፡ ወራት፡ ይመጣል አለ፤
ወይትካፈሉ፡ በርበረኪ፡ በውስቴትኪ፣
ምርኮሽን፡ አሕዛብ፡ ይካፈሉታል፤

፪፤ ወአስተጋብዖሙ፡ ለኵሎሙ፡
አሕዛብ፡ ይትቃተልዋ፡ ለኢየሩሳሌም፣
ኢየሩሳሌምን፡ ያጠፏት፡ ዘንድ፡
አሕዛብን፡ እሰበስባቸዋለሁ፤
ወትትቀተል፡ ሀገር፣
ኢየሩሳሌም፡ ትጠፋለች፤
ወይትበረበር፡ ቤት፣
ቤቱ፡ ኹሉ፡ ይበዘበዛል፤
ወይረኵሳ፡ አንስት፣
ወይዛዝርቱ፡ ይረክሳሉ፣ ያለ
ፈቃዳቸው፡ አሕዛብ፡ እየሳቡ፡

ወይፄወዉ፡ መላህቅተ፡ ሀገር፣
የሀገር፡ አለቆች፡ ይማረካሉ፤
ወእለተርፉ፡ ሕዝብየ፡ ኢይጠፍኡ፡ እም
ሀገሮሙ፣
ከሞት፡ የቀሩት፡ ወገኖች፡ ከሀ
ገራቸው፡ አይጠፉም፣

፫፤ ወይወጽእ፡ እግዚአብሔር፡ ወይ
ትቃተሎሙ፡ ለእሙንቱ፡ አሕዛብ፡ ከመ፡
አመ፡ ዕለተ፡ ቀትል፣
እግዚአብሔር፡ በመዓት፡ ይመ
ጣል፣ እንደ፡ ግብፅ፡ ጊዜ፡ ሰልፍ፡
በተደረገበት፡ ቀን፡ እነዚያን፡
አሕዛብን፡ ያጠፏቸዋል፤

፬፤ ወይቀውማ፡ እገሪሁ፡ ውእተ፡
አሚረ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ ዘይት፣
ያን፡ ጊዜ፡ የአንጥያኮስ፡ እግ
ሮቹ፡ በደብረ፡ ዘይት፡ ይቆማሉ፤
ዘቅድመ፡ ኢየሩሳሌም፡ ጽባሒሃ፣
ምሥራቅነቷ፡ በኢየሩሳሌም፡
አንፃር፡ የሆነ፤
ወይነቅዕ፡ ደብረ፡ ዘይት፣
የአንጥያኮስ፡ ጦሩ፡ ይከፈላል፤
መንፈቁሂ፡ መንገለ፡ ጽባሕ፡ ወባሕር፣
እኩሌታው፡ ወደምዕራብ፡ እኵ
ሌታው፡ ወደምሥራቅ፡ ይሄዷል፤
ወይትቈለቈል፡ መንፈቁ፡ ለውእቱ፡
ደብር፡ መንገለ፡ ደቡብ፣
እኩሌታው፡ ወደ፡ ደቡብ፡
ይሄዳል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይከውን፡ ዓቢየ፡ ጸድፈ፤

ጽኑ፡ መከራ፡ ይደረጋል፤

ወመንፈቁሂ፡ ለሰሜን፤

እኩሌታው፡ ወደ፡ ሰሜን፡ ይሄዳል፤

፭፤ ወይትሐፀር፡ ቈላተ፡ አድባርየ፤

ቆላውም፡ ደጋውም፡ በጦር፡ ይታጠራል፤ አንድም፡ ወይቀውማ፡ እገሪሁ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ያን፡ ጊዜ፡ የጌታ፡ እግሮቹ፡ በደብረ፡ ዘይት፡ ይቆማሉ፤ ምሥራቅነቷ፡ በኢየሩሳሌም፡ አንፃር፡ የሆነ፤ ወፈነዎሙ፡ በበ፪ቱ እንዲል፤ ሐዋርያትን በየሀገሩ፡ ሁለት፡ ሁለቱን፡ ይሰዳቸዋል፤ እኩሌታው፡ ወደምሥራቅ፤ እኩሌታው፡ ወደምዕራብ፡ ይሄዳሉ፤ በደቡብም፡ ያስተምራሉ፤ ብዙ፡ ምስጢር፡ ይገለጣል፤ ትምህርቱ፡ በአራቱ፡ ማዕዘን፡ ይነገራል፤ ቆላውም፡ ደጋውም፡ በትምህርት፡ ይታጠራል፤

አንድም፡ ወይቀውማ እገሪሁ፡ የጥጦስ፡ የሐሳዊ፡ መሲሕ፡ እግሮቹ፡ በደብረ፡ ዘይት፡ ይቆማሉ፤ ምሥራቅነቷ፡ በኢየሩሳሌም፡ አንፃር፡ የሆነ፡ ጥጦስ፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ጦሩን፡ እየከፈለ፡ በአራቱ፡ ማዕዘን፡ ይሰ

በጥጦስ፡ በሐሳዊ መሲሕ፡ ጊዜ፡ ቆላውም፡ ደጋውም፡ በጦር፡ ይታጠራል፤

ወይበጽሕ፡ እስከ፡ ኢያሶን፤

ጦሩ፡ እስከ፡ ኢያሶን፡ ይደርሳል፤

ከመ፡ አመ፡ ተፈጸመ፡ መዋዕለ፡ ድልቅልቅ፡ በመዋዕለ፡ ዖዝያን፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፤

በይሁዳ፡ ንጉሥ፡ በዖዝያን፡ ዘመን፡ ንውጽውፅታ፡ ያለው፡ ቀን፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፤ አንድም፡ ንውጽውጽታው፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፤ አንድም፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ ንውጽውጽታው፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፤

ወይመጽእ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኪየ፡ ወኵሎሙ፡ ቅዱሳን፡ ምስሌሁ፤

ፈጣሪየ፡ እግዚአብሔር፡ ይመጣል፡ ቅዱሳን፡ መላእክት፡ ኹሉም፡ ከሱ፡ ጋራ፡ ይመጣሉ፤

፮፤ ወይእቲ፡ አሚረ፡ አልባ፡ ብርሃን፤

ይሁዳ፡ መቅብያዊ፡ የሞተባት፡ ቀን፡ ተድላ፡ ደስታ፡ የለባትም፤ አንድም፡ ጌታ፡ የሞተባት፡ ቀን፡ ተድላ፡ ደስታ፡ የለባትም፤

ወትከውን፡ አሐተ፡ ዕለት፡ ቍረ፡ ወበረደ፤

ይሁዳ፡ መ...



ትሆናለች፤ አንድም፡ ጌታ፡ የሞተባት፡ አንዲት፡ ቀን፡ በረድ፡ ቅዝቃዜ፡ ትሆናለች፤ አንድም፡ ጌታ፡ የተሰቀለባት፡ ዕለተ፡ ዓርብ፡ በረድ፡ ቅዝቃዜ፡ ትሆናለች፤

፯፤ ወይእቲ፡ ዕለት፡ ዕምርት፡ በኀበ፡ እግዚአብሔር፤

ይህች፡ ይሁዳ፡ መቅብያዊ፡ የሞተባት፡ ቀን፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የታወቀች፡ ናት፤ አንድም፡ ይኽች፡ ጌታ፡ የተሰቀለባት፡ ዕለተ፡ ዓርብ፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የታወቀች፡ ናት፤

ወኢኮነት፡ መዓልተ፤

ብርሃን፡ አልሆነችም፤ ይሁዳ፡ መቅብያዊ፡ ሙቷልና፤

ወኢኮነት፡ ሌሊተ፤

ጨለማ፡ አልሆነችም፡ አለ፤ መቃብያንን፡ ታናሽ፡ ወንድሙ፡ ይዟቸው፡ ወጥቷልና፤ አንድም፡ ኢኮነት፡ መዓልተ፡ ጌታ፡ የተሰቀለባት፡ ቀን፡ ብርሃን፡ አይደለችም፤ ከቀትር፡ እስከ፡ ዘጠኝ፡ ሰዓት፡ ጨለማ፡ ኹኗልና፤

ወኢኮነት፡ ሌሊተ፤

ጨለማም፡ አልሆነችም፤ በሠርክ፡

ወፍና፡ ሠርክ፡ ይበርህ፡ ብርሃነ፡ ፀሐይ፤

በሠርክ፡ ጊዜ፡ ብርሃነ፡ ፀሐይ፡ ያበራ፡ ነበረ፤

፰፤ ወውእተ፡ አሚረ፡ ይወጽእ፡ ማየ፡ ሕይወት፡ እምኢየሩሳሌም፤

ያንጊዜ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ማየ፡ ሕይወት፡ ይመነጫል፤

መንፈቁ፡ መንገለ፡ ባሕር፡ ቀዳሚት፡ ወመንፈቁ፡ መንገለ፡ ባሕር፡ ደኃሪት፤

ከፊት፡ በር፡ እስከ፡ ኋላ፡ ዳረገንድ፡ ይፈስሳል፤ አንድም፡ ይወጽእ፡ ማየ፡ ሕይወት፡ ብለህ፡ መልስ፤ ከነቢያት፡ ትንቢት፤ ከካህናት፡ ትምህርት፡ ይገኛል፤ በዐሥሩ፡ ነገድ፡ በሁለቱ፡ ነገድ፡ ይነገራል፤ አንድም፡ ትምህርት፡ ለሕዝብ፡ ለአሕዛብ፡ ይሰጣል፤ አንድም፡ ማየ፡ ሕይወት፡ ከጌታ፡ ጎን፡ ይፈስሳል፤ ጥምቀት፡ በአካለ፡ ሥጋ፤ በአካለ፡ ነፍስ፡ ላሉ፡ ይሰጣል፤

ወከማሁ፡ ይከውን፡ በክረምት፡ ወበሐጋይ፤

አሁን፡ እንደተናገርኹት፡ ትምህርት፡ በክረምት፡ በበጋ፡ ይደረጋል፤ አንድም፡ በነቢያት፡

www.ethiopianorthodox.org

በካህናት፡ በኦሪት፡ በወንጌል፡ ይነገራል።

፱፡ ወይነግሥ፡ እግዚአብሔር፡ ለኵሉ፡ ምድር።

እግዚአብሔር፡ በዓለሙ፡ ኹሉ፡ ነግሦ፡ ይኖራል።

ወይእተ፡ አሚረ፡ ይከውን፡ አሐዱ፡ እግዚአብሔር።

ያንጊዜ፡ ፈጣሪ፡ እሱ፡ ብቻ ይሆናል።

ወአሐዱ፡ ስሙ።

የሱ፡ ስም፡ ብቻ፡ ሲጠራ፡ ይኖራል።

፲፡ ወይበጽሕ፡ ኵሎ፡ ምድረ።

በዓለሙ፡ ሁሉ፡ ይነገራል።

ወየዓውድ፡ ገዳመ፡ እምጌላቡሄ፡ እስከሬማ።

ከጌልቡሄ፡ ጀምሮ፡ እስከሬማ፡ ድረስ፡ የጌታ፡ ስሙ፡ ሲጠራ፡ ይኖራል።

ወእምደቡባሂ፡ ለኢየሩሳሌም።

ከኢየሩሳሌም፡ ደቡብ፡ ጀምሮ፡ ስሙ፡ ሲጠራ፡ ይኖራል።

ወሬማሰ ትነብር፡ ውስተ፡ ብሔራ።

ሬማ፡ ግን፡ ጠላት፡ ጠፍቶ ላት፡ ጸንታ፡ ትኖራለች።

እምአንቀጸ፡ ብንያም፡ እስከ፡ አንቀጸ፡ ደወለ፡ ጸናፊ፡ አንቀጸ፡ መዓዝን።

ከብንያም፡ በር፡ ጀምሮ፡ አራት፡ መዓዝን፡ እስካለው፡ በር፡ አው ራጃ፡ ድረስ፡ የጌታ፡ ስም፡ ይጠራል።

ወእስከ፡ ማኅፈደ፡ አናምሄል።

አናምሄል፡ ስመ፡ ሀገር፡ ነው።
አንድም፡ የሰው፡ ስም፡ ነው።
እስከ፡ አናምሄል፡ ግምብ፡ ድረስ፡ ስሙ፡ ይጠራል።

ወእስከ፡ ምክያደ፡ ዘቤተ፡ ንጉሥ፡ ይነብርዋ።

የንጉሥ፡ ወገኖች፡ ፈረስ፡ እስ ከሚሞክሩበት፡ ድረስ፡ ስሙ፡ ይጠራል።

፲፩፡ ወኢትከውን፡ እንከ፡ ውግዘተ።

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ተለይታ፡ አትጠፋም።

ወትነብር፡ እንከ፡ ተአሚና፡ ኢየሩሳሌም።

ኢየሩሳሌም፡ ጠላት፡ ጠፍቶ ላት፡ አርፋ፡ ትኖራለች።

፲፪፡ ወዛቲ፡ ይእቲ፡ ድቀቶሙ፡ እንተ፡ ይመትሮሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ ተቃተልዋ፡ ለኢየሩሳሌም።

እግዚአብሔር፡ ኢየሩሳሌምን፡ ያጠፏት፡ አሕዛብን፡ ያጠፋቸው፡ ጥፋት፡ ይች፡ ናት።

ወይትመሰው፡ ሥጋሆሙ፡ እንዘ፡ ይቀ ውሙ፡ በእገሪሆሙ።

በእግራቸው፡ ቁመው፡ ሳሉ፡ ሥጋቸው፡ እንደሰም፡ ይቀ ልጣል።



ወይውኅዝ፡ አዕይንቲሆሙ፡ እምው ስተ፡ ግበቢሆሙ።

ዓይናቸው፡ ከመቃዳቸው፡ ይወጣል።

ወይትመሰው፡ ልሳኖሙ፡ በውስተ፡ አፉሆሙ።

የነአንጥያኮስ፡ አንደበታቸው፡ ከአፋቸው፡ ይጠፋል። ቁስለ፡ ሥጋ፡ ታሞ፤ አንደበቱ፡ ተቆርጦ፡ ሙቷልና።

፲፫፡ ወይከውን፡ ይእተ፡ አሚረ፡ ዓቢይ፡ ድንጋፄ፡ ላዕሌሆሙ፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር።

ያንጊዜ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ታዝዞ፡ ጽኑ፡ ድንጋጤ፡ ይመ ጣባቸዋል።

ወይእኀዝ፡ ፩ዱ፡ ፩ዱ፡ እደ፡ ካልዑ።

ከጎግ፡ ማጎግ፡ ወገን፡ አንዱ፡ አንዱን፡ ይይዘዋል።

ወትጠግዕ፡ እዴሁ፡ በእደ፡ ካልኡ።

አንዱ፡ በአንዱ፡ እጅ፡ ይጠፋል።

፲፬፡ ወይትቃተሉ፡ በይሁዳ፡ ወበ ኢየሩሳሌም።

በይሁዳ፤ በኢየሩሳሌም፡ ይዋጋሉ።

ወያስተጋብዑ፡ ኃይለ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፡ ዘዓውዳ።

በዙሪያዋ፡ ያሉ፡ የአሕዛብን፡ [illegible] ያደርጋሉ።

ወርቀ፡ ወብሩረ፡ ወአልባሰ፡ ብዙኃ፡ ፈድፋደ።

ወርቁን፡ ብሩን፡ ልብሱን፡ አብ ዝተው፡ ይሰበስባሉ።

፲፭፡ ወዛቲ፡ ይእቲ፡ ድቀተ፡ አፍ ራሲሆሙ፡ ወአብቅሊሆሙ፡ ወአግማ ሊሆሙ፡ ወአዕዱጊሆሙ።

የፈረሶቻቸው፡ የበቅሎዎቻቸው፡ የግመሎቻቸው፡ ያህዮቻቸው፡ ጥፋት፡ ይኽ፡ ነው።

ወኵሉ፡ እንስሳሆሙ፡ ዘሀሎ፡ ውስተ፡ ትዕይንቶሙ።

በከተማቸው፡ ያለ፡ የእንስሳው፡ ሁሉ፡ ጥፋት፡ ይኽ፡ ነው።

ወከመዝ፡ ውእቱ፡ ድቀቶሙ።

ጥፋታቸው፡ ይህ፡ ነው።

፲፮፡ ወኵሎሙ፡ እለ፡ ተርፉ፡ እም ኵሉ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ መጽኡ፡ ላዕለ፡ ኢየሩሳሌም።

ከሞት፡ የቀሩቱ፡ አሕዛብ፡ ወደ ኢየሩሳሌም፡ የመጡቱ።

የዓርጉ፡ በበዓመት፡ ይስግዱ፡ ለንጉሥ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ ፈጣሪያቸው፡ ለሚሆን፡ ለእግዚአብሔር፡ ይሰ ግዱ፡ ዘንድ፡ በዓመት፡ በዓመት፡ ይወጣሉ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ፡ ይግበሩ፡ በዓለ፡ መጸለት፤

በዓለ፡ መጸለትን፡ ያከብሩ፡ ዘንድ፡ ይወጣሉ፤

፲፯፤ ወኵሉ፡ ዘኢዐርገ፡ እምኵሉ፡ ምድር፡ ውስተ፡ ኢየሩሳሌም፡ ከመ፡ ይስግዱ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ ለሚገዛ፡ ለእግዚአብሔር፡ ይሰግዱ፡ ዘንድ፡ ከአሕዛብ፡ ወገን፡ ወደኢየሩሳሌም፡ ያልወጣ፡ ይጠፋል፤

ወእለሂ፡ ይትዌሰኩ፡ ዲበ፡ እልክቱ፤

አሁን፡ የተናገርናቸው፡ እነዚህ፡ እነበጥሊሞስ፡ እነእስክንድር፡ አምነው፡ ይጨመራሉ፤ አንድም፡ ሴት፡ በባሏ፡ ወንድ፡ በሚስቱ፡ ተስበው፡ በቀሩ በእስራኤል፡ ላይ፡ አማንያን፡ አሕዛብ፡ ለበዓል፡ ባይወጡ፡ ይጠፋሉ፤

፲፰፤ ወእመሂ፡ ሕዝበ፡ ግብፅ፡ ኢዐርጉ፡ ወኢመጽኡ፡ ህየ፡ ይከውን፡ ላዕሌሆሙ፡ ድቀት፤

የግብፅ፡ ሰዎች፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ባይወጡ፡ መከራ፡ ይመጣባቸዋል፤

ወዘይቀሥፎሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለኵሉ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ ኢዐርጉ፡ ይግበሩ፡ በዓለ፡ መጸለት፤

በዓለ፡ መጸለትን፡ ያከብሩ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ያልወጡ፡ አሕዛብን፡ እግዚአብሔር፡ ያጠፋቸዋል፤

፲፱፤ ወዛቲ፡ ይእቲ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለግብፅ ወኃጢአቶሙ፤ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ ኢዐርጉ፡ ይግበሩ፡ በዓለ፡ መፀለት፤

የግብፅ፡ ሰዎች፡ የአሕዛብ፡ ኃጢአታቸው፡ በዓለ፡ መፀለትን፡ ያከብሩ፡ ዘንድ፡ አለመውጣታቸው፡ ነው፤

፳፤ ወውእቱ፡ አሚረ፡ ይከውን፡ ልጓመ፡ ፈረስ፡ ቅዱሰ፤ ለእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ያን፡ ጊዜ፡ የጎግ፡ የማጎግ፡ ገንዘብ፡ ለእግዚአብሔር፡ የተለየ፡ ገንዘብ ይሆናል፤

ወይከውና፡ ጻሕራት፡ ውስተ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ኮራት፡ ቅድመ፡ ገጹ፡ ለምሥዋዕ፤

እንስራዎች፡ በምሥዋዐ፡ ፊት፡ በቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እንዳሉ፡ ጋኖች፡ ይሆናሉ፤

፳፩፤ ወይሄልዋ፡ ጻሕራት፡ ዘውስተ፡ ምሥዋዕ፡ ዘኢየሩሳሌም፡ መቅደሱ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

በምሥዋዕ፡ ያሉ፡ እንስራዎች፡ በኢየሩሳሌም፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ ይኖራሉ፤

ወይመጽኡ፡ ኵሎሙ፡ ወይሠውዑ፤

ሁሉም፡ መ[illegible]



ወይነሥኡ፡ እምውስቴቶሙ፡ ወያበስሉ፡ ቦቶን፤

ከነዚያ፡ እያመጡ፡ ይቀቅሉባቸዋል፤

ወኢይትረከብ፡ እንከ፡ ይእተ፡ አሚረ፡ ከነናዊ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ያንጊዜ፡ ሁሉን፡ በሚገዛ፡ በእግዚአብሔር፡ ማደሪያ፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ አንድ፡ አረማዊ፡ አይገኝም፤ አንድም፡ ወይእተ፡ አሚረ፡ ይከውን፡ ልጓመ፡ ፈረስ፡ ቅዱሰ፡ ለእግዚአብሔር፡ ብለህ፡ መልስ፤ መናፍቃን፡ በጠፉ፡ ጊዜ፤ አንድም፡ ቆስጠንጢኖስ፡ በነገሠ፡ ጊዜ፡ የፈረሱ፡ ልጓም፡ ልዩ፡ ይሆናል፡ አለ፤ በፈረሱ፡ ፊት፤ በጦሩ፡ አንደበት፤ በጋሻው፡ እንብርት፤ ለምልክት፡ ትእምርተ፡ መስቀል፡ አድርጎ፡ አሠርቶታልና፤

ወአግበረት፡ ዕሌኒ፡ ንግሥት፡ ልጓመ፡ ፈረስ፡ ለንጉሥ፡ እንዲል፤ እናቱ እያሠራች፡ ምልክት፡ ሰዳለታለች፤ ዲያቆናት፡ እንደቀሳውስት፡ ይሆናሉ፤ ቀሳውስት፡ እንደኤጲስ፡ ቆጶሳት፡ ይሆናሉ፤ ሰዎች፡ ሁሉ፡ እየመጡ፡ ይናዘዙባቸዋል፤ ቀሳውስትም፡ ይናዝዟቸዋል፤ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሰይጣን፡ አይገኝም፤

ተፈጸመ፡ ዘዘካርያስ፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ የሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤

አነሣስቶ፡ ለአስጀመረን፤ አስጀምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፤ አሜን፤ በእውነት፡፡

www.ethiopianorthodox.org